# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

83ኛ ዓመት ቁጥር 010 መስከረም 10 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









# መንግሥት ከመጠባበቂያ መጋዘኑ የሁለተኛ ዙር ሰብዓዊ ድጋፍ ለማድረግ በዝግጅት ላይ ነው

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- መንግሥት ከመጠባበቂያ መጋዘኑ በሀገሪቱ በተለያዩ አካባቢዎች አፋጣኝ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው አራት ሚሊዮን ዜጎች የሁለተኛ ዙር ሰብዓዊ ድጋፍ ለመስጠት በዝግጅት ላይ መሆኑን የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን አስታወቀ።

የኮሚሽኑ የሕዝብ ግንኙነት ከፍተኛ ባለሙያ አቶ አታለለ አቡሀይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የአሜሪካ ተራድኦ ድርጅትና አጋር አካላት በኢትዮጵያ ለተወሰኑ ወራት ምግብ ነክና ሌሎችንም ሰብዓዊ ድጋፎች ማቋረጣቸውን ተከትሎ መንግሥት ክፍተቶችን ለመሙላት ከራሱ መጠባበቂያ የምግብ ክምችት መጋዘኖች ወጪ አድርጎ በመጀመሪያው ዙር ለአራት ሚሊዮን ዜጎች ድጋፍ አድርጓል። በተመሳሳይ መልኩ በሁለተኛ ዙር ለአራት ሚሊዮን ዜጎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ድጋፉን ለመስጠት በዝግጅት ላይ ይገኛል።

ኮሚሽኑ ድጋፎችን የሚያደርገው በየ45ቀኑ እንደሆነ የገለጹት አቶ አታለል፤ አጋር አካላት እርዳታ ማድረግ ካቆሙበት ጊዜ ጀምሮ መንግሥት ክፍተቱን ለመሙላት እየሠራ እንዳለ ጠቁመዋል።

አቶ አታለለ፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ ባለፉት ጊዜያት ለአራት ሚሊዮን የሚጠጉና በሁሉም አካባቢ ላሉ ዜጎች መንግሥት


መንግሥት ከመጠባበቂያ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል







# ከመንገዶች ክፍያ አገልግሎት አንድ ነጥብ 54 ቢሊዮን ብር ለማግኘት ታቅዷል

## - ከደረሱ 771 የትራፊክ አደጋዎች 77 ሞት ተመዝግቧል

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- ከአዲስ አበባ - አዳማ፣ ከድሬዳዋ-ደወሌ እና ከሞጆ - ባቱ ከመንገዶች ክፍያ አገልግሎት አንድ ነጥብ 54 ቢሊዮን ብር ለማግኘት ማቀዱን የኢትዮጵያ ክፍያ መንገዶች ኢንተርፕራይዝ ገለጸ።

የኢንተርፕራይዙ ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ዐብይ ወረታው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኢንተርፕራይዙ በመንገዶች ክፍያ አገልግሎት በ2015 ዓ.ም 733 ሚሊዮን ብር ገደማ ለማግኘት አቅዶ 798 ሚሊዮን ያህል ብር አግኝቷል። በአዲሱ ዓመትም ከመንገዶች ክፍያ አገልግሎት አንድ ነጥብ 54 ቢሊዮን ብር ለማግኘት ታቅዷል።

በ2016 ዓ.ም የታሪፍ ማሻሻያ ተግባራዊ ለማድረግ ጥናት ላይ እንገኛለን ያሉት አቶ ዐብይ፤ በሶስቱ የክፍያ ጣቢያዎች ማለትም ከአዲስ አበባ - አዳማ፣ በድሬዳዋ-


ከመንገዶች ክፍያ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል










# ከ51 ሺህ በላይ ከስደት ተመላሾች ሥልጠና ወስደው ወደ ሥራ ሊሰማሩ ነው

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- ከ51ሺህ በላይ ከስደት ተመላሾች ሥልጠና በመስጠት ወደ ሥራ ለማስገባት እየተሠራ መሆኑን የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ። ከ37ሺህ በላይ ለሆኑ ዜጎች ከነቤተሰቦቻቸው የኑሮ ማሻሻያ ድጋፍ እንደተደረገላቸው ተገልጿል።

በሚኒስቴሩ የሕገወጥ ሰዎች ዝውውር መከላከልና የተመላሽ ዜጎች ድጋፍና ክትትል መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ደረጀ ተግይበሉ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በ2015 ዓ.ም በሁለት ዙሮች ከሳውዲ አረቢያ 134 ሺህ ዜጎች ወደ ሀገራቸው መመለስ ተችሏል። ከ51ሺህ በላይ የሆኑ ከስደት ተመላሾች ለሥራ የሚያስፈልጋቸውን ሥልጠና በመስጠት ወደ ሥራ እንዲሰማሩ እየተደረገ ነው።

ከስደት ከተመለሱት ውስጥ ስድስት ሺዎቹ ሕፃናት ሲሆኑ፤ የተቀሩት ከ18 እስከ 35 ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ዜጎች ናቸው ያሉት አቶ ደረጀ፤ ከ51ሺህ በላይ የሆኑ ከስደት ተመላሾች ለሥራ የሚያስፈልጋቸውን ሥልጠና በመስጠት ወደሥራ እንዲገቡ እየተደረገ መሆኑን አመልክተዋል።

ለስደት ተመላሽ ዜጎቹ ለሥራ መነሻ የሚሆን


ከ51 ሺህ በላይ ከስደት... ወደ ገጽ 6 ዞሯል




አቶ ሽመልስ አብዲሳ

# በክልሉ በመጪው ክረምት አምስት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ችግኞች ለመትከል ዕቅድ ተይዟል

**ጌትነት ምህረቴ**

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል በመጪው ክረምት በአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር አምስት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ችግኞች ለመትከል ዕቅድ መያዙን የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ ገለጹ። በክልሉ በተጠናቀቀው


በክልሉ በመጪው ክረምት ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል









# የጌዲዮ መልክዓ ምድር በዓለም ቅርስነት መመዝገቡ በዞኑ የቱሪስት ፍሰት እንዲጨምር ያደርጋል

ሞገስ ተስፋ

አዲስ አበባ፡- የጌዲዮ ዞን መልክዓ ምድር አቀማመጥ በዓለም ቅርስነት መመዝገቡ በዞኑ የቱሪስት ፍሰት እንዲጨምር በማድረግ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚያስገኝ መሆኑን የጌዲዮ ዞን ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ገለጸ። በዞኑ ያሉ የቱሪስት መስህቦችን በዓለም ቅርስነት ለማስመዝገብ እየተሠራ መሆኑ ተገልጿል።

በጌዲዮ ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ የኮሙዩኒኬሽንና ኢንፎርሜሽን ባለሙያ አቶ ዳንኤል ከተማ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ዞኑ ቀደምት አባቶች በሀገር በቀል እውቀታቸው በመጠቀም የመሬት አያያዝ፣ ደንና የቅርሶች አጠባበቅ፤ ከአምስት ሺ ዓመታት በላይ ተንከባክበው ያቆዩት አኩሪ ታሪክ ነው። ይህ መልክዓ ምድር በዓለም ቅርስነት መመዝገቡ በዞኑ የቱሪስት ፍሰት እንዲጨምር ያደርጋል።

የዞኑ ሕዝብ ከጥንት ጀምሮ ዛፍን ያለመቁረጥ፣ አንድ ሲቆርጡ በምትኩ ሁለት ዛፍ የመትከል ልምድና ባህል አለው ያሉት አቶ ዳንኤል፤በደራሮ ወይም በዘመን መለወጫ ዓመታዊ በዓል ላይ ደን እንዳይቆረጥ፤ ልማት እንዲስፋፋ፣ በየአካባቢው ያሉ ሀገር በቀል ዕውቀቶች


የጌዲዮ ዞን መልክዓ ምድር አቀማመጥ

እንዲዳብሩና ባህሉ ተጠናክሮ እንዲቀጥል አዋጅ ይተላለፋል። ሕዝቡ አዋጁን ተቀብሎ ወደ ተግባር የመለወጥ ልምድ ያዳበረ መሆኑን ገልጸዋል።

በዞኑ በርካታ ተፈጥሯዊ፣ ታሪካዊ፣ ባህላዊ ቅርሶችን የቱሪስት መዳረሻዎና መስህቦች እንደሚገኙ የገለጹት የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያው፤ መስህቦቹ በስፋት እንዲታወቁ ዞኑ ከክልሉና ከፌዴራል ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በቁርጠኝነት ሠርቷል ብለዋል።

በምስራቅ አፍሪካ ከሚገኙት 10 ሺ ትክል ድንጋዮች መካከል ከስድስት ሺ በላይ የሚሆነው ትክል ድንጋዮች በጌዲዮ ዞን ብቻ እንደሚገኝ ገልጸው፤ ዞኑ ውስጥ የሚገኙ ቅርሶችን ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ለማስተዋወቅ የሀገርህን እወቅ ክበባትና የተለያዩ የማስተዋወቂያ አማራጮችን በመጠቀም በተሠራው ሥራም የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ቱሪስቶች ዞኑን እንዲጎበኙ ተደርጓል ነው ያሉት።

እንደ አቶ ዳንኤል ማብራሪያ፤ ከሰሞኑ በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት የሳይንስና እና የባህል ድርጅት /ዩኔስኮ/ በዓለም ቅርስነት የተመዘገበው የጌዲዮ መልክዓ ምድር በፌዴራል ቅርስና ጠበቃ ባለስልጣንና የክልሉ ባህልና ቱሪዝ ቢሮ በጋራ በመሆን ጥናት ላይ በመመስረት ባከናወኑት ሥራ ነው። በኢትዮጵያ 10ኛ ሆኖ የተመዘገበው መልክዓ ምድር በዞኑ ያሉ ሌሎች የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ መስህቦች በቱሪስቶች እንዲጎበኙ ትልቅ በር የሚከፍት ነው።

በጌዲዮ ዞን የባህላዊ አስተዳደር ሥርዓት፣ የዳኝነት ሥርዓት፣ ባህላዊ የግጭት አፈታትና የደራሮ በዓልን በዩኔስኮ ለማስመዝገብ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ስለመሆኑ አቶ ዳንኤል ገልጸዋል።



ፎቶ፡- ገበቦ ገብሬ

# የንግዱ ማኅበረሰብ በኢትዮጵያ የሚካሄዱ ዓለም አቀፍ የንግድ ትርኢቶችን በአግባቡ ሊጠቀም ይገባል

## -አዲስ ቻምበር ሦስት ዓለም አቀፍ የንግድ ትርኢቶችን ለማካሄድ ዝግጅቱን እያጠናቀቀ ነው

ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት በሚያዘጋጃቸው ዓለም አቀፍ ንግድ ትርኢቶች ላይ የንግዱ ማኅበረሰብ በንቃት በመሳተፍ የሚፈጠሩ መልካም አጋጣሚዎችን አሟጠው ሊጠቀሙ እንደሚገባ ተገለጸ። ምክር ቤቱ በያዝነው 2016 ዓ.ም ሦስት ዓለም አቀፍ የንግድ ትርኢቶችን ለማካሄድ ዝግጅቱን እያጠናቀቀ መሆኑንም አስታውቋል።

የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት መሰንበት ሸንቁጤ ከትናንት ወዲያ በሰጡት መግለጫ እንዳሉት፤ ምክር ቤቱ ባለፉት በርካታ ዓመታት ዓለም አቀፍ የንግድ ትርኢትና ባዛሮችን በማዘጋጀት ንግድና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ የበኩሉን ሚና ሲወጣ ቆይቷል። በዚህ ዓመት በሚካሄዱ ዓለም አቀፍ ንግድ ትርኢቶችም ከተለያዩ ሀገራት የሚመጡ በርካታ ድርጅቶች ስለሚሳተፉ የንግዱ ማኅበረሰብ አጋጣሚውን በአግባቡ እንዲጠቀም ጥሪ አቅርበዋል።

ምክር ቤቱ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ የንግድ ትርኢቶችን በማዘጋጀትና ሌሎችንም ንግድና ኢንቨስትመንትን የሚያበረታቱ ተግባራትን ሲያከናውን መቆየቱን የጠቀሱት ፕሬዚዳንቷ፤ በ2016ዓ.ም የሚዘጋጁት ንግድ ትርኢቶች ግብርና፣ ምግብ፣ ማኑፋክቸሪንግና ቴክኖሎጂ ላይ የሚያተኩሩ መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

የንግዱ ማኅበረሰብም እነዚህን ንግድ ትርኢቶች በመጠቀም ምርትና አገልግሎትን በማስተዋወቅ፣ ገበያ በማፈላለግ፣ የቴክኖሎጂ ልውውጥ በማድረግ፣ የሥራ አጋርነትን በማጠናከርና ለዜጎች የሥራ እድል በመፍጠር እንዲጠቀምባቸው ነው የገለጹት።

በእነዚህ ንግድ ትርኢቶች ላይ የንግዱ ማኅበረሰብ በንቃት በመሳተፍ የሚፈጠሩ እድሎችን አሟጠው መጠቀም ይገባቸዋል ብለዋል።

የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ለንግዱ ማኅበረሰብ ምቹ የሥራ ሁኔታ ለመፍጠር ትኩረት አድርጎ እንደሚንቀሳቀስ አስታውሰው፤ ኢትዮጵያ ብሪክስን መቀላቀሏን ተከትሎ ሊፈጠሩ የሚችሉ መልካም አጋጣሚዎችን ለመጠቀም ጥናት እያደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

የምክር ቤቱ ዋና ፀሐፊ አቶ ሺበሺ ቤተማርያም በበኩላቸው፤ እንደ ሀገር በተለያዩ ችግሮች ውስጥ ብንሆንም የንግድ መስፋፋትና የኢኮኖሚ ልማት መጠናከር ለብዙ ችግሮች መፍትሔ ናቸው ነው ያሉት።

ምክር ቤቱ ንግድና ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት፣ የሥራ እድል ለመፍጠር፣ የውጭ ምንዛሪ የሚያስገኙ ተግባራትን ለማከናወን የሚያስችሉ እድሎችን ሁሉ በአግባቡ መጠቀም ያስፈልጋል ብለዋል።

በዚህ ዓመትም 26ኛው አዲስ ቻምበር ዓለም አቀፍ የንግድ ትርኢት፣ 14ኛው የግብርናና ምግብ ንግድ ትርኢትና 6ኛውን የማኑፋክቸሪንግና ቴክኖሎጂ ንግድ ትርኢቶችን ለማካሄድ ዝግጅቶች በመጠናቀቅ ላይ መሆናቸው ተገልጿል።

የግብርናና ምግብ ንግድ ትርኢት ከህዳር 27 እስከ ህዳር 29 ቀን 2016 ዓ.ም፣ አዲስ ቻምበር ዓለም አቀፍ ንግድ ትርኢት ከየካቲት 14 እስከ የካቲት 18 ቀን 2016ዓ.ም እንዲሁም የማኑፋክቸሪንግና ቴክኖሎጂ ንግድ ትርኢት ከግንቦት 15 እስከ ግንቦት 19 ቀን 2016 ዓ.ም እንደሚካሄድ ተጠቁሟል።

# የወባ በሽታን ለመከላከል በ40 ሚሊዮን ዶላር ወጪ የአጎበር ግዥ በመፈጸም ማሰራጨት ተችሏል

ሞገስ ጸጋዬ

አዲስ አበባ፡- በ2015 በጀት ዓመት ኢትዮጵያ በ40 ሚሊዮን ዶላር ወጪ 19 ነጥብ 5 ሚሊዮን የአጎበር ግዥ በመፈጸም ለኅብረተሰቡ ማሰራጨቱን የጤና ሚኒስቴር አስታወቀ።

የጤና ሚኒስቴር የወባ በሽታ መከላከልና መቆጣጠር መሪ

ሥራ አስፈጻሚ ዶክተር ህይወት ሰለሞን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ በኢትዮጵያ በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ ምክንያቶች ለወባ ስርጭት ምቹ ሁኔታዎች እየተፈጠረ ነው። ስርጭቱን ለመቀነስ ብዙ ሥራዎች ተሠርተዋል። በ2015 በጀት ዓመት በ40 ሚሊዮን ዶላር ወጪ 19 ነጥብ 5 ሚሊዮን የመኝታ አጎበር በወባ ተጠቂ በሆኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች እንዲሰራጭ ተደርጓል።

የወባ ስርጭትን ለመቆጣጠርና ለመከላከል የወባ አጎበር ከማደል ጎን ለጎን ወባማ አካባቢዎች ላይ የተመረጡ ቤቶችን ርጭት ማካሄድ፣ ምርምርና ጥናት ማድረግና የግንዛቤ ፈጠራ ሥራ መሥራቱን ጠቅሰዋል።

75 በመቶ የኢትዮጵያ የቆዳ ስፋት ለወባና ለትንኝ ወለድ በሽታዎች ምቹ መራያቢ ነው ያሉት መሪ ሥራ አስፈጻሚዋ፤ ኢትዮጵያ የወባ ስርጭት ካለባቸው ሀገራት መካከል የምትመደብ ናት። የወባ ስርጭት በተወሰነ መልኩ መቀነሱን ተከትሎ በኅብረተሰቡ የመዘናጋት፣ የአካባቢ ቁጥጥር ሥራንና የመኝታ አጎበርን በትክክል ያለመጠቀም ሁኔታ በጉልህ ይታያል ብለዋል።

ችግሩን ለመፍታትም የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን በሚገባ የማስፋት ሥራ መሥራቱን ጠቁመው፤ የታማሚ ምጣኔ ቢጨምርም የሞት ቁጥር ቀደም ሲል ባለበት እንዲቆም ማድረግ መቻሉን ጠቅሰዋል።

የስርጭት ምጣኔው ከቦታ ቦታ ቢለያይም ስርጭቱን ለመቀነስ በተሰራ ሥራ በወሳኝ መለኪያዎች ውጤት አምጥተናል ያሉት ዶክተር ህይወት፤ለዚህም የዓለም የጤና ድርጅትም እውቅና ሰጥቶታል። የሞት ምጣኔንና የታማሚ ቁጥርን ከመቀነስ አንጻር እ.ኤ.አ በ2020 የተቀመጠውን ትልም በማሳካት ኢትዮጵያ ከጥቂት ሀገራት መካከል አንዷ መሆኗን አውስተዋል።


ዶክተር ህይወት ሰለሞን

እንደ ዶክተር ህይወት ገለጻ፤ባለፉት ሦስት ዓመታት ከፍተኛ የሆነ የአየር ንብረት ለውጥ በመከሰቱ ወባና ትንኝ ወለድ የሆኑ በሽታዎች ለመስፋፋት ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል። ኢትዮጵያን ጨምሮ በአፍሪካ ሀገራትና በዓለም ደረጃ ሞቃታማ አካባቢዎች ከፍተኛ የሆነ ስርጭት ተስተውሏል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተወሰነ መዘናጋት ቢኖርም በተሰሩ ሥራዎች በወባ ላይ ብዙ ለውጥ ማምጣት መቻሉን መሪ ሥራ አስፈጻሚዋ አንስተው፤ ኢትዮጵያ የወባ በሽታን ስትቆጣጠር ከ60 ዓመታት በላይ አሳልፋለች። በተለይ የትንኝ ቁጥጥር ሥራ ላይ የመኝታ አጎበርን በማሰራጨት፣ የቤት ውስጥ ርጭትን በማካሄድና የትንኝ እጭዎችን በመቆጣጠር ብዙ ውጤቶች ማምጣት መቻሉን ጠቅሰዋል።

ኅብረተሰቡ ስለ ወባ ያለው አመለካከት እንዲስተካከል የግንዛቤ ሥራ በመሥራትና የጤና ኤክስቴንሽን አገልግሎት በማስፋፋት በወባ ቁጥጥር ላይ ውጤት ለማምጣት ቁልፍ የሆነ አስተዋጽኦ ሲያደርግ መቆየቱንም አውስተዋል።

በጥናቶች መሠረት 96 በመቶ የወባ ሞትና የታማሚዎች ቁጥር የሚመዘገበው በአፍሪካ አህጉር መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ።



አቶ ግርማ ገመቹ

# ኢትዮጵያ 98 በመቶ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦቷን ከታዳሽ ኃይል እያገኘች ነው

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ከ98 በመቶ በላይ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦቷን ከታዳሽ ኃይል እያገኘች መሆኑን የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን አስታወቀ።

በአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ ሕግ ተከባሪነት ዳይሬክተር ጄነራል አቶ ግርማ ገመቹ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ከውሃ ግድቦች፣ ከእንፋሎት(ከጂኦተርማል)፣ ከንፋስና ከፀሐይ ኃይል በምታገኘው የኤሌክትሪክ ኃይል አማካኝነት ከአካባቢ ብክለት ነፃ የሆነ ውጤታማ ሥራ እያከናወነች ይገኛል።

ከሀገሪቷ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ከ98 በመቶ በላዩ ከታዳሽ ኃይልን እንደሚያገኝ የተናገሩት አቶ ግርማ፤ ባለፉት ዓመታት በሀገሪቱ ታዳሽ ኃይልን እንደ ኃይል አማራጭ ለመጠቀም በተሠሩ ሥራዎች ውጤት መመዝገቡን ጠቁመዋል።

የዓባይ ግድብንና ሌሎች ትላልቅ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ግድቦች ጨምሮ ታዳሽ ኃይልን በማመጨት ረገድ ወሳኝ ድርሻ እየተወጡ መሆኑን አመልክተዋል።

አቶ ግርማ እንደገለጹት፤ ሀገሪቱ ታዳሽ ካልሆነ ኃይል በተለይም የነዳጅ ጄኔሬተሮችን በመጠቀም የምታሰራጨው የኤሌክትሪክ ኃይል አነስተኛ በመሆኑ ከአካባቢ ጥበቃ አንጻር የሚበረታታ ተግባር ነው።

የአዳማ ነፋስ ኃይል የኤሌክትሪክ ማመንጫ እና በሥራ ላይ የሚገኙ የእንፋሎት ኃይል ማመንጫዎች የአየር ብክለትን ለመከላከል የሚደረገውን ጥረት ለመደገፍ የሚረዱ መሆናቸውን አስረድተዋል።

ዳይሬክተር ጄኔራሉ እንዳመለከቱት፤ በአሁኑ ወቅት ዓለምን እያስጨነቁ ከሚገኙ ነገሮች መካከል አንዱና ዋነኛው የአየር ንብረት ለውጥ ችግር ነው። ለዓለም አየር ንብረት ለውጥ መንስኤ እየሆነ ያለው ታዳሽ ያልሆኑ የኃይል አማራጮችን መጠቀም ነው፤ በተለይ ያደጉ ሀገራት የድንጋይ ከሰልንና ሌሎች የነዳጅ ምንጮችን በመጠቀም የሚያከናውኗቸው ግንባታዎችና ፕሮጀክቶች የአካባቢ ብክለትን እያባባሰ ይገኛል።

ኢትዮጵያ ተግባራዊ ካደረገቻቸው የአረንጓዴ አሻራ መርሀ-ግብሮች በተጨማሪ የታዳሽ ኃይልን አማራጭ ለማስፋት የምታደርገው ጥረት በዓለም አቀፍ ደረጃም ዕውቅና እያስገኘላት ነው ብለዋል።

ታዳሽ ኃይልን በብዛት መጠቀም የብዝሀ ሕይወት መመናመን እንዳይስፋፋ ይረዳል ያሉት አቶ ግርማ፤ ታዳሽ ኃይል በብዛት መጠቀም እያሳሰበ የሚገኘውን የአየር ንብረት ለውጥ ለመከላከል ጉልህ ሚና እንደሚጫወት ተናግረዋል።

አቶ ግርማ እንዳመለከቱት፤ መረጃዎች እንደሚያሳዩት በአፍሪካ ባለፉት 50 ዓመታት 65 በመቶ የሚሆነው የብዛ ሕይወት ተመናምኗል። ችግሩን ለመከላከል በዘርፉ ከሚከናወኑ ሳይንሳዊ ሥራዎች ባለፈ የአካባቢ ብክለትን የማያስከትሉ ታዳሽ የኤሌክትሪክ ኃይሎችን መጠቀም ይገባል።

የታዳሽ ኃይል መጠቀም ከአካባቢ ብክለትና ከብዝሀ ሕይወት ጉዳት ጋር ተያይዞ የሚከሰቱ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ቀውሶችን ለመከላከል ዓይነተኛ አማራጭ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

# በክልሉ ከ11 ቢሊዮን ብር በላይ ካፒታል ያስመዘገቡ ባለሀብቶች ወደ ሥራ ገብተዋል

## - ከ12 ሺ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

አዲስ አበባ፡- በሶማሌ ክልል ከ11 ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር በላይ ያስመዘገቡ ባለሀብቶች በተለያዩ የኢንቨስትመንት መስኮች ሥራ መጀመራቸውን የክልሉ ኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ቢሮ አስታወቀ። ለ12ሺ 243 ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር መቻሉን ተጠቁሟል።

በቢሮው የኢንቨስትመንት ማስታወቂያና ማስፋፊያ ዳይሬክተር አቶ አብዲአዚዝ አሕመድ በተለይ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደተናገሩት፤በክልሉ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ክልል ከ11 ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር በላይ ያስመዘገቡ ባለሀብቶች በተለያዩ የኢንቨስትመንት መስኮች ሥራ ጀምረዋል። በዘርፉ የተመዘገበው ውጤት ከታቀደው አንጻር ከፍተኛ ነው። ይህም ሊሆን የቻለው በክልሉ ሰላም በመስፈኑና ለኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር በመቻሉ ነው ብለዋል።

በበጀት ዓመቱ አዲስ የኢንቨስትመንት ፈቃድ የወሰዱ ባለሀብቶች ቁጥር 367 መሆናቸውን አውስተው፤ ከዚህ ውስጥ 37 የሚሆኑት በውጭ ሀገራት የሚኖሩ የክልሉ ተወላጆች መሆናቸውን አመልክተዋል።

በአዲሱ በጀት ዓመት ይህንን አጠናክሮ ለመቀጠል በተለያዩ ሀገራት የሚኖሩ የክልሉ ተወላጆችን መረጃ የማጠናቀር ስሥራ እየተሠራ እንደሚገኝ ገልጸው፤



አቶ አብዲአዚዝ አሕመድ፤

በተጨማሪም ወደ ክልሉ መጥተው በኢንቨስትመንት ሲሰማሩ የሚገጥማቸውን ችግር ለማቃለልም የዲያስፖራ አገልግሎት መስጫዎችን በአንድ ማዕከል እንዲያገኙ ለማድረግ ከተለያዩ አስፈፃሚ መስሪያ ቤቶች ጋር በመነጋገር የተቀላጠፈ አገልግሎት እንዲያገኙ እየተሠራ ይገኛል ብለዋል።

በዘርፉ እየተሰጡ ያሉ አገልግሎቶችን ቀልጣፋና ከወቅቱ ጋር የሚራመዱ ለማድረግም የፌዴራል የኢንቨስትመንት አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎችን መሠረት በማድረግ የክልሉ የኢንቨስትመንት ማስፈፀሚያ መመሪያዎችና ደንቦች እንዲሻሻሉ ተደርጓል ነው ያሉት።

በኢንዱስትሪው ዘርፍም በሀገር አቀፍ ደረጃ እየተካሄደ ያለው የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ መርሀ ግብርን በመጠቀም የአምራች ኢንዱስትሪዎች አቅም በማሳደግ፣ በሀገር አቀፍ ደረጃና በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ ለማድረግ በርካታ ሥራዎች ተከናውነዋል ያሉት አቶ አብዲአዚዝ፣ ይህንኑ ኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ሂደትን በተፈለገው መንገድ ለማስኬድና ውጤታማ ለማድረግም 40 ከሚሆኑ ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት መካሄዱን ጠቁመዋል።

ለኢንዱስትሪ መንደር ተብሎ የተዘጋጀ ቦታን ለባለሀብቶች ለማስተላለፍ አስፈላጊ መሠረተ ልማቶችን የማጠናቀቅ ሥራዎች መሠራታቸውን አንስተው፤ በቀጣይም ተጨማሪ የኢንዱስትሪ መንደር የማዘጋጀት ሥራዎች የሚከናወኑ ይሆናል ብለዋል።

ባለሀብቶች በኢንዱስትሪው ዘርፍ ቢሰማሩ ልማት ባንክ ያዘጋጀውን የፕሮጀክት ፋይናንሲንግ እድል ተጠቃሚ የሚሆኑበትን አካሄድ አስመልክቶም ውይይቶች መካሄዳቸውን ገልጸዋል።

# የመስቀልና የኢሬቻ በዓላት እሴታቸውን ጠብቀው እንዲከበሩ ሁሉም የበኩሉን ኃላፊነት ሊወጣ ይገባል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- የመስቀልና የኢሬቻ በዓላት እሴታቸውን ጠብቀው እንዲከበሩ ሁሉም የበኩሉን ኃላፊነት ሊወጣ እንደሚገባ የሃይማኖት አባቶችና አባ ገዳዎች ገለጹ።

የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ እና በሸገር ከተማ አስተዳደር የኮዬ ፈጬ ክፍለ ከተማ የመስቀልና የኢሬቻ በዓላት በሰላም እንዲከበሩ የጋራ የምክክር መድረክ በትናንትናው ዕለት አካሂደዋል።

በምክክር መድረኩ ላይ ተሳታፊ የነበሩት የቂሊንጦ መንበረ ብርሀን ቅድስት ስላሴ ቤተክርስቲያን ዋና አስተዳዳሪ መላከ ሰላም ቀሲስ አበበ መለሰ እንዳሉት፤ መስቀል እየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጅ ሰላም ሕይወቱን የከፈለበት፣ ሰላም የታወጀበት በዓል ነው። በዓሉ ሲከበርም ሰላማዊ በሆነ መንገድ ሊሆን ይገባል።

የመስቀል በዓል ሲከበርም ሁሉም ምእመን ሰላም የሕይወት እስትንፋስ መሆኑን በመገንዘብ ሰላምን የሚጠሉ ሰዎች ቢኖሩም የሰላም ዘብ በመሆን በዓሉ ሃይማኖታዊ ሥርዓቱን በጠበቀ መልኩ እንዲከበር ማድረግ እንደሚኖርበት ገልጸዋል።

ቀሲስ አበበ ኢትዮጵያውያን የተለያየ ማንነት፣ ቋንቋና እምነት ቢኖራቸውም፤ ኢትዮጵያዊነታቸው አንድ ያደርጋቸዋል። ሃይማኖታዊ በዓላት እሴታቸው ተጠብቆ እንዲከበር ሁሉም የበኩሉን ኃላፊነት ሊወጣ ይገባል ብለዋል።

ሌላኛው በውይይቱ ተሳታፊ የነበሩት የገዳ ምክር ቤት አማካሪ ሽጉጤ ገላ፤ ኢሬቻ የሚከበረው አምላክ ክረምቱን አሳልፎ ፀሐዩን ስላሳየ ነው። ይህ በዓል በንጹህ ልቦና ምስጋና የሚቀርብበት ነው። የተጣላ ታርቆ ሁሉም ሰው በሰላማዊ መንገድ ሊያከብረው እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

ኢሬቻ ወንድማማችነት የሚገለጽበት አንዱ መንገድ ነው ያሉት አማካሪው፤ ልዩነትን ከማጉላት ይልቅ ሁሉም በመከባበርና የአንዱን ባህል አንዱ በመቀበል ሊያከብረው እንደሚገባ ገልጸዋል።



ኢሬቻ የሰላም ፣የፍቅር፣ የይቅርታ በዓል ሆኖ ሳለ ይህንን ለማጠልሸት የሚንቀሳቀሱ አካላት ቢኖሩም ሁሉም በቃ ሊላቸው እንደሚገባ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

የኮዬ ፈጬ ክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ፍቃዱ ቱሉ፤ በመስከረም ወር የሚከበሩት የመስቀል እና የኢሬቻ በዓላት የሕዝብ ሕዝብ ግንኙነትን ለማጠናከርና በዓላቶቹን ሰላማዊ በሆነ መንገድ እሴታቸውን ጠብቀው እንዲከበሩ የኅብረተሰቡ አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው ብለዋል።

አቶ ፍቃዱ የመስቀል በዓል ሃይማኖቱ በሚፈቅደው መልኩና የኢሬቻም በዓል የገዳ ሥርዓቱን በተከተለ መልኩ እሴቱን ጠብቆ ያለምንም የፀጥታ ችግር ሊከበር ይገባዋል ብለዋል።

ሁለቱም በዓላት የዓለም ቅርስ ሆነው በዩኔስኮ የተመዘገቡ መሆናቸውን ገልጸው፤ በዓላቱ የተወሰነ ማኅበረሰብ ብቻ ሳይሆኑ የመላው ዓለም መሆናቸውን በመገንዘብ ማክበር ይገባል ነው ያሉት። በዓላቶቹ እሴታቸውን ጠብቀው እንዳይከበሩ የሚንቀሳቀሱ አካላት ማኅበረሰቡ በጋራ ሊከላከላቸውና ለሕግ አካላት ሊያጋልጣቸው እንደሚገባ አሳስበዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የትምህርት ሥርዓቱን እየተፈተነ ካለበት ዘርፈ ብዙ ችግሮች ስመታደግ!

በብዙ ፈተናዎች ውስጥ ያለውን የሀገሪቱን የትምህርት ጥራት ለማሻሻል ባለፉት ሁለት ዓመታት ሰፊ ሥራዎች ተሠርተዋል። ተስፋ ሰጪ ውጤቶች እየተመዘገቡ ነው። ከእነዚህም ውስጥ በትምህርት ሚኒስቴር ተቋማዊ ለውጥ ማምጣት የሚያስችሉ የሪፎርም ሥራዎችን ከማስጀመር አንስቶ፤ የትምህርት ፖሊሲዎችን የመከለስ ሥራዎች ተካሂደዋል።

ለሀገራዊ የትምህርት ጥራት ተጠቃሽ የሆነውን ኩረጃ ባህል ለማስቀረት የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ ፈተና በዩኒቨርሲቲዎች እንዲሰጥ፣ የዩኒቨርሲቲ ተመራቂ ተማሪዎችም የመውጫ ፈተና እንዲወስዱ ተደርጓል። የመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎችም ራስ ገዝ የሚሆኑበት የሕግ ማዕቀፍ ተግባራዊ ሆኗል።

በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አዲስ ሥርዓተ ትምህርት ተግባራዊ ሆኗል። በመላው ሀገሪቱ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ለመማር ማስተማር ሂደቱ ውጤታማ እንዲሆኑ ለማስቻል ሀገራዊ የሕዝብ ንቅናቄ በመፍጠር ደረጃቸውን ለማስተካከል ትልቅ ሥራ ተሠርቷል። የወላጅ ተማሪ መምህር ኅብረትም (ወተመህ) በአዲስ የኃላፊነት መንፈስ ወደ ሥራ የተገባበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

ትምህርት ሚኒስቴር የትምህርት ጥራትን በማረጋገጥ በሥነምግባር የታነፀ ፣ ለሀገርና ለሕዝብ ብሩህ ነገዎች ተስፋ የሚጣልበት ትውልድ ለመገንባት ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ የሚገኘው ዘርፈ ብዙ ሥራ፣ ተስፋ ሰጪ ስለመሆኑም በተጨባጭ እየተስተዋለ ነው።

በርግጥ የኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓት የደረሰበት ውድቀት ከሀገር ህልውና ጥያቄ የሚተናነስ አይደለም፡፡ ይህንን ትልቅ ሀገራዊ ስብራት ለመጠገን ትምህርት ሚኒስቴር እንደ ተቋም የጀመረው ሁለንተናዊ ጥረት የመላው ሕዝባችን ይሁንታ የተቸረው ነው ።ይህንን የሕዝብ አጋርነት አሚጦ መጠቀም ከቻለ በዘርፉ ትልቅ ታሪክ መሥራት እንደሚ ያስችለው ይታመናል።

በኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓት ላይ ለሚታየው ስብራት አንዱ በተማሪዎች ላይ የሚታየው ከራስ ጥረትና ልፋት ይልቅ በሌሎች ትከሻ ወረቀትን ለማግኘት የሚደረግ ሩጫ ነው፡፡ ይህን መጥፎ ልምድ ሥር እየሰደደ እንዳይሄድ መንግሥት ከጀመረው አበረታች ርምጃዎች በተጨማሪ የተማሪዎችና የወላጆች እንዲሁም የመምህራን ሚና የላቀ ነው፡፡

ትምህርት ሚኒስቴርም ችግሩን ለመቅረፍ የፈተና አሰጣጥ ሥርዓቱን ከማሻሻል ጀምሮ ሌሎች አቋራጭ የኩረጃ መንገዶችን ለመዝጋት የጀመራቸውን ሥራዎች በአዲሱ የትምህርት ዘመን አጠናክሮ መቀጠል ይጠበቅበታል። በዚህም በሀገሪቱ የትምህርት ሥርዓት የገነገነውን የኩረጃ ባህል ታሪክ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

ሕዝቡ አሁን ላይ ለትምህርቱ ዘርፍ የፈጠረውን የባለቤትነት መንፈስ የበለጠ በማጠናከር የጀመረውን የፋይናንስና የማቴሪያል ድጋፍ በማሳደግ ትምህርት ቤቶችን ፣ ተጨማሪ ክፍሎችን እንዲገነባ ፣ ነባሮቹንም እንዲያድስ ፣ የትምህርት ግብአቶችን በማሟላት ረገድ ተገቢውን ተሳትፎ እንዲያደርግ የሚያስችሉ ሕዝባዊ ንቅናቄዎችን በቀጣይም መፍጠር ይጠበቅበታል፡፡

የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ እየተደረገ ያለው ሀገራዊ ጥረት ውጤታማ እንዲሆን ፤የትምህርት መዋቅሩ አስተማማኝ ይሆን ዘንድ በተጠናከረ ሁኔታ ተደራጅቶ ወደ ሥራ የገባው የወላጅ ተማሪ መምህር ኅብረት (ወተመህ) ሊበረታታ ይገባል፡፡ ወላጆች ልጆቻቸውን ጥራት ያለው ትምህርት እንዲያገኙ የሚያሳዩትን ፍላጎት እውን ለማድረግ በትምህርት ሥራው ላይ በቀጥታ እንዲሳተፉ ማድረግም ያስፈልጋል፡፡

በየጊዜው ትምህርት ቤቶች ተፈላጊውን የብቃት ደረጃ ማሟላታቸውን በመገምገም ብቃታቸው ለተረጋገጠላቸው ብቻ በኃላፊነት ዕውቅና እንዲያገኙ፤ ችግር ያለባቸው ዕድሳት እያገኙ አቅማቸውን የሚገነቡበት ሕጋዊነት ያለው ሥርዓት መዘርጋት ፤ በትምህርት ተቋማት መካከል መልካም የውድድር መንፈስ እንዲፈጠር የሚያስችል አሠራርም መፍጠር ተገቢ ነው፡፡

በዚህም የትምህርት ተቋማት ደረጃ ምደባና ሞዴል ትምህርት ቤቶችን በጥራት የመምረጥና ዕውቅና የመስጠት፣ ከተፈላጊው ደረጃ በታች የሆኑ ትምህርት ቤቶችን ክፍተታቸውን በማሳየት በቀጣይ ወደ ተሻለ ደረጃ መድረስ እንዲችሉ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ተፈላጊ ግብ የሆነውን የተማሪዎችን ውጤትና ሥነምግባር ማሻሻል ያስፈልጋል።

በአጠቃላይ የሀገሪቱ የትምህርት ሥርዓት እየተፈተነ ካለበት ዘርፈ ብዙ ችግሮች ለመታደግ በቀደሙት ዓመታት የተጀመሩ በተለይም ከጥራት ጋር የተያያዙና ተስፋ ሰጪ ሥራዎችን በዚህም ዓመት በጠንካራ ተቋማዊ እና ሕዝባዊ አቅም ማስቀጠል ያስፈልጋል፤ለዚህም ከወዲሁ በቂ ዝግጅትና ቁርጠኝነት መፍጠር ወሳኝ ነው!


**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ከዲጅታሳይዜሽን በስተጀርባ ሳሉ ተግዳሮቶች ትኩረት እንስጥ

ትንሳኤ አበራ

አዲሱ ዓመት ለሀገራችን የሰላም ፣ የፍቅር፣ የአንድነትና የብልጽግና እንዲሆንልን ተመኝተን ዓመቱን በመልካም ምኞት አሃዱ ብለን መጀመራችን እሰየው የሚያሰኝ ነው። ምኞታችን ምኞት ብቻ ሳይሆን እውን ሆኖ ወደ ተግባር እንዲቀየር ማድረግ ደግሞ የሁሉም ኃላፊነት ነው ። ከዚህ የተነሳም እያንዳንዱ ዜጋ ለራሱም ሆነ ለሀገሩ ብሩህ ነገዎች ከእኔ ምን ይጠበቃል የሚለውን ጠይቆ በሚገባ ማወቅ ይጠበቅበታል ።

በተለይም እንደሀገር ባሳለፍነው ዓመት አላሰራ ብለው ወደኋላ ሲጎትቱን የነበሩ አሠራሮች ምንድናቸው ብሎ ፤ እነሱን አሻሽሎና አዘምኖ በማስቀጠል ጥሩ ውጤት እንዲመዘገብ ማስቻል የአዲሱ ዓመት ትልቁ የቤት ሥራ ሊሆን ይገባል ፤ በተለይም እንደ ሀገር የተጀመረው የዲጅታላይዜሽን ሥርዓቶችን ክፍተቶች አርሞ አጠናክሮ ማስቀጠል ተገቢ ነው ።

አንድ የአሠራር ሥርዓት (ሲስተም) ሲዘረጋ ሥራን በፈጠነ ሁኔታና በአጭር ጊዜ በማከናወን አገልግሎት አሰጣጥ ለማቀላጠፍ እንዲረዳ ታስቦ ነው። ይህ ደግሞ ጊዜ፣ ጉልበትና አላስፈላጊ ወጪን በማስቀረት ተገልጋይን ከእንግልት የሚታደግ አሠራር ነው። ይህን የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት ብቻ ሳይሆን ምን ያህል ችግሮች መቅረፍ ችሏል። እንዴትስ ነው ተግባራዊ እየተደረገ ያለው የሚሉትን ጉዳዮች ማየት ያስፈልጋል።

አሁን ላይ በአብዛኛው በመንግሥት የሚሰጡ አገልግሎቶች ወደ ዲጅታላይዜሽን አሠራር ሥርዓት (በሲስተም) እየተቀየሩ ነው ፤ እነዚህን የአሠራር ሥርዓቶች ቆም ብለን መፈተሽ ተገቢ ነው በትራንስፖርት ፣ በጤና ፣ በትምህርት እና በሌሎችም ዘርፎች አገልግሎቶች ዲጅታላይዝድ እየሆኑ ነው ።

በርግጥ አገልግሎቶችን ዲጅታላይዜሽን ማድረግ በራሱ ግብ አይደለም ። ግቡ በአጭር ጊዜ ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት መስጠት ነው ። ለዚህ ደግሞ ዲጅታላይዝድ የተደረገ አገልግሎትን በየጊዜው መገምገም እና በሚያጋጥሙ ችግሮች ዙሪያ የማስተካከያ ርምጃዎችን መውሰድ ወሳኝ ነው። ይህንን በተመለከተ አገልግሎት ፍለጋ ሄጄ ያጋጠመኝን ዝብርቅርቅ ላካፍላችሁ።

አሁን ላይ በመዲናችን የሚገኙ አብዛኛው ጤና ተቋማት አገልግሎታቸውን ዲጅታላይዝድ እያደረጉ ነው። በተለይ በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች በየቀኑ የሚያስተናግዱ ጤና ጣቢያዎች ላይ አሠራሩ ተግባራዊ መደረጉ ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት እንደሚረዳ ይታመናል።

እግር ጥሎኝ የሄድኩበት የጤና ጣቢያ ያጋጠመኝ ግን ከዚህ የተለየ ነው ፤የቀደመውን የማንዋል አሠራር የሚያስናፍቅ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ይህ ሃሳብ ደግሞ በወቅቱ አገልግሎቱን ፈልገው የመጡ ሰዎችም ሃሳብ እንደሆነ እንዲታወቅ እፈልጋለሁ።

ቀደም ሲል በማንዋል በሚሠራበት ወቅት አንድ ሰው ጤና ጣቢያ ገብቶ አገልግሎቱን አግኝቶ የሚሄድበት ሰዓትና አሁን አገልግሎቱ ዲጅታላይዝድ ከተደረገ በኋላ ያለው ሁኔታ ፈጽሞ አይገኛኝም።‹‹ትሻልን ትቼ ትብስን አገባሁ›› አይነት ሆኖ እርፍ ብሏል።

በእለቱ የነበረው የሰው ብዛት ወረፋም ለጉድ ነበር።አንድ ሰው ቅድሚያ ካርድ ክፍል ደርሶ ካርድ ለማውጣት በትንሹ 20 ደቂቃ ይፈጅበታል። ቀጥሎ ደግሞ ህክምና ወደ የሚያገኝበት ክፍል ወረፋ ደርሶት ለመመርመር ብቻ ቢያንስ 40 ደቂቃ ይወስዳል። ተያያዥ ምርመራዎች ከታዘዙለትማ አገልግሎቱን ለማግኘት ምን ያህል ጊዜ ሊፈጅበት እንደሚችል በቀላሉ ማሰብ ይቻላል።

ታዲያ በትንሹ ስናሰላው ለአንድ ሰው ከካርድ ክፍል ተነስቶ ምርመራ ክፍል ያለውን ሂደት ጨርሶ ለመውጣት ብቻ አንድ ሰዓት ያህል ጊዜ ያስፈልገዋል ማለት ነው። ይህንን ካለው የህዝብ ብዛት አንጻር ስናሰላው ደግሞ ነገሩን “ከድጡ ወደ ማጡ” እንዲሉት አይነት ያደርገዋል። ይህ የሚሆነው ደግሞ እግዜር ረድቷችሁ ሲስተሙ እስካልተቋረጠ ድረስ ነው። ሲስተሙ ከተቋረጠ ደግሞ እስከሚመጣ ድረስ የሚፈጀውን ጊዜ ማሰብ አይከብድም።

አጋጣሚ ሆኖ በሄድኩበት ቀን መብራት መጥፋቱን ተከትሎ ሲስተሙ ተቋረጠ። ይህ የሆነው አምስት ሰዓት ከሩብ ላይ ሲሆን ከትንሽ ቆይታ በኋላ መብራት ቢመጣም ሲስተሙ ሊመጣ አልቻለም። ከዚያ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ባለሙያዎች ባደረጉት ጥረት ተሳክቶላቸው ለስድስት ሰዓት አምስት ጉዳይ ላይ ሲስተሙ ቢስተካከልም አገልግሎት የሚሰጡት ሠራተኞች ደግሞ በቦታቸው የሉም፤ ለምሳ ወጥተዋል።

ለህመሙ ፈውስን ፈልጎ ደጃቸውን የረገጠው ህብረተሰብ ከህመሙ ጋር እየታገለ ከምሳ እስኪመለሱ መጠበቁ የግድ ሆኖበት ቢጠብቅም ከሰዓት እነሱ እንደገቡ ሲስተሙ በድጋሚ እልም አለ። ምሬታቸውን መቆጣጠር ያልቻሉ አንዳንድ ሰዎች ጥያቄ ቢያቀርቡም ሲስተሙ አልመጣም እኛ ምን እናድርግ የሚል ምላሽን ብቻ ነው ማግኘት የቻሉት።

ሲስተሙ መጣሁ! ጠፋሁ! የሚል ከሆነ ህሙማኑን ለማስተናገድ የሚያስችል ሌላ አማራጭ መኖር ነበረበት። በሌላ በኩል ደግሞ ሲስተሙም እያለ ቢሆንም አንድ ሰው ለማስተናገድ የሚወስደው ጊዜ ይህንን ያህል መርዘሙ ለምን አስፈለገ የሚሉት ጥያቄዎች ናላዬን ቢያዞሩት ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ሠራተኞች እና ኃላፊዎች ማነጋገር መርጥኩ። ከትንሽ ቆይታ በኋላ እንደገና በማንዋል እየተመዘገበ አገልግሎት እንዲሰጥ ተደረገ።

ከዚያ ቀን በፊት ባሉት ቀናት ግን እንደዚህ አይነት ችግር አጋጥሞ አገልግሎቱን ሳያገኙ ወደቤታቸው የተመለሱ ሰዎች እንዳሉ ማረጋገጥ ችያለሁ። በድጋሚ በአዲሱ ዓመት መጀመሪያ ወደ ተቋም የምመለሰበት አጋጣሚ ቢፈጠርም በዕለቱ ሲስተም ባይጠፋም አሠራሩ ግን ፍጥነት የሌለው እንደነበር መመልከት ችያለሁ።

በሌላ አጋጣሚ በትራንስፖርት ዘርፉም ላይ እንዲሁ አጋጥሞኛል ፤ እንደሚታወቀው ከአዳማ አዲስ አበባ ያለውን የትራንስፖርት አሰጣጥ ዲጅታላይዝድ ለማድረግ የተደረገው ጥረት ችግር ከመቅረፍ ይልቅ ለሌብነትና ለብልሹ አሠራር በር ከፋች መሆኑን መመልከት ችያለሁ። አዲሱ አሠራር ህዝቡን ለረጃጅም ሰልፍ፣ ለእንግልትና ለአላስፈላጊ ወጪ እየዳረገው ይገኛል።

የትራንስፖርት ትኬት ለመቁረጥ ያ ሁሉ ህዝብ ወረፋ እየጠበቀ ሳለ እዚያው መናኸሪያ ውስጥ ያሉ ሃይ ባይ ያጡ መኪኖች ለአንድ ሰው 200 መቶ ብር በማስከፈል ከዚያ ጭነው ሲወጡ ይታያል። ታዲያ ሲስተም መዘርጋቱ ለምን አስፈለገ ያሰኝም?።

ይህ ከሲስተም ጋር ተያይዞ የሚታይ ብዙ ችግሮች መኖራቸውን ያሳየናልና ሊታሰብበት ይገባል። እንደተረዳሁት ከሆነ ጎልቶ የታየው የሲስተሙ ችግር ሳይሆን ሲስተሙን ላይ የሚሠራው የሰው ኃይል የኮምፒውተር አጠቃቀም ችግርና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ናቸው።

በሁሉቱም ዘርፎች ብዙ ተገልጋይ ያላቸው ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ያለው ችግር በሚገባ ተጠንቶ ስር ሳይሰድ እልባት ሊሰጠው ይገባል ። ለዚህ ደግሞ የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ኃላፊነታቸው መወጣት አለባቸው ፤አበቃሁ።

ዜና




# ኢትዮጵያ ከኩባ ጋር ያላትን የትብብር አድማስ በማስፋት የሁለትዮሽ ግንኙነቱን ለማጠናከር እየሠራች ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ ፡- ኢትዮጵያ ከኩባ ጋር ያላትን የትብብር አድማስ በማስፋት የሁለትዮሽ ግንኙነቱን ለማጠናከር እየሠራች መሆኑን በኩባ የኢትዮጵያ አምባሳደር ገነት ተሾመ ገለጹ።

አምባሳደር ገነት ሁለቱ ሀገራት ለረጅም ጊዜ የዘለቀ ወዳጅነትና ትብብር እንዳላቸው ገልጸው፤ ኩባ በተለይም ለኢትዮጵያ በርካታ ድጋፎችን ማድረጓን ጠቁመዋል።

የኩባ ወታደሮች ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት መስዋዕትነት መክፈላቸውን አስታውሰው፤ ይህ ውለታ በኢትዮጵያውያን ዘንድ የሚረሳ አይደለም ብለዋል።

ኩባ በሺዎች ለሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን የትምህርት እድል መስጠቷንም ጠቁመዋል።

ያም ብቻ ሳይሆን የኩባ የሕክምና ባለሙያዎች በኢትዮጵያ ለሚገኙ የዘርፉ ባለሙያዎች የትምህርትና የሥልጠና ድጋፍ እየሰጡ መሆኑን አመልክተዋል።

ኩባ በግብርና፣ ውሃሀብት ልማት፣ በመስኖ፣ አካባቢ ጥበቃና በተለያዩ መስኮች ያላትን ልምድ ለኢትዮጵያ ለማካፈል እንደምትሻም ገልጸዋል።

የሁለቱ ሀገራትን የሁለትዮሽ ግንኙነት ለማጠናከር ሳይንስና ቴክኖሎጂን ጨምሮ በተለያዩ የትብብር መስኮች አጋርነቱን ለማስፋት እየተሠራ መሆኑን ኢዜአ ዘግቧል።

በቅርቡ በኩባ መዲና ሃቫና በተካሄደው የቡድን 77 እና ቻይና ጉባኤ፤ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን የተመራ የኢትዮጵያ ልዑክ ቡድን መሳተፉ ይታወሳል።

ከጉባኤው ጎን ለጎን አቶ ደመቀ ከኩባ ፕሬዚዳንት ሚጉዌል ቤርሙዴዝ ፈርናንዴዝና ከሌሎች የሀገሪቱ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ጋር የሁለቱን ሀገራት አጋርነት ለማጠናከር በሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ መክረዋል።

ኢትዮጵያና ኩባ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነታቸውን የጀመሩት እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1975 ነው።

## በክልሉ በመጪው ክረምት...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ክረምት የተተከሉትን 4 ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ችግኞችን ሕዝቡ መንከባከብ እንደሚኖርበትም ጠቁመዋል።

የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ እንደገለጹት፤ በኦሮሚያ ክልል በመጪው ክረምት በአረንጓዴ አሻራ አምስት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ችግኞች ለመትከል ዕቅድ ተይዟል።ይህን ዕቅድ ለማሳካት ከወዲሁ ዝግጅት ተጀምሯል። ለዚህ የሚያስፈልጉ የችግኝ ዘሮች እየተዘጋጁ ነው። የችግኝ ጣቢያዎችን መልሶ የማደስ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ።

በተጠናቀቀው ክረምት በክልሉ 4 ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ችግኞች ተተክለዋል ያሉት አቶ ሽመልስ፤ በአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብሩ በከተማና በገጠር ያለው ሕዝብ ከጫፍ ጫፍ የተሳተፈበት በመሆኑም ጥሩ ውጤት የተመዘገበበት ነው ብለዋል።

በክልሉ በ2014 ዓ.ም የተተከሉ ችግኞችን በአግባቡ የመንከባከብ ሥራ መሠራቱን አመልክተው፤ የተተከሉ ችግኞች የጽድቀት መጠንም 87 በመቶ መድረሱን ተናግረዋል።

ክልሉ የፍራፍሬ ችግኞች በዓይነትና በብዛት መተከላቸውን ገልጸው፤ ይህም ለግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች ጥሬ ዕቃ በቀላሉና በሚፈልጉት ልክ እንዲያገኙ የሚያስችላቸው መሆኑን አመልክተዋል።

አረንጓዴ አሻራ ከተጀመረ ጀምሮ እስካሁን ድረስም ከዚህ በፊት በክልሉ ተጎድተውና ምድረ በዳ የሆኑ አካባቢዎች እያገገሙና በአረንጓዴ እየተሸፈኑ መምጣታቸው ነው የገለጹት።

የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ከአካባቢ ጥበቃ ባለፈ ለበርካታ ወጣቶች የሥራ ዕድል እየፈጠረና የምግብ ዋስትናንም በማረጋገጥ ረገድ ጉልህ ሚና እየተጫወተ ነው ያሉት።

ይህም ሕዝቡ የአረንጓዴ አሻራ አጀንዳን የራሱ ስላደረገው እና ትንሽ ትልቅ፣ የገጠር የከተማ ሳይል በነቂስ በመውጣት ችግኝ እየተከለና እየተንከባከበ በመሆኑ የተመዘገበ ውጤት መሆኑን ገልጸዋል።

የአረንጓዴ አሻራ ያለምንም ችግር እየተሳካ ያለ ሀገራዊ መርሀ ግብር ነው ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብም በዚህ መርሀ ግብር ታሪክ መሥራት እንደሚችል ያሳየበት ነው። ይህን አኩሪ ታሪክም ችግኞችን በመንከባከብና በመጠበቅ አጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ጥሪ አቅርበዋል።

## ከ51ሺህ በላይ ከስደት ተመላሾች...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ካፒታልና የመሥሪያ ቦታ ተመቻችቶላቸዋል ያሉት አቶ ደረጀ፤ በተለያዩ መስኮች ሥራ የጀመሩ ዜጎች መኖራቸውን ተናግረዋል። ዜጎቹ ተመልሰው ወደ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እንዳይገቡ መንግሥት ሀገር ውስጥ ያሉ የሥራ ዕድሎችን በመጠቀም መለወጥ የሚችሉበትን ሁኔታ ሲያመቻች መቆየቱን አቶ ደረጀ አስታውሰዋል።

ከስደት ተመላሽ ዜጎችን በማኑፋክቸሪንግ፣ በንግድ፣ በምግብ ዝግጅትና በተለያዩ ዘርፎች እንዲሰማሩ እየተደረገ መሆኑ ተጠቁሟል።

የቀጥታ ድጋፍ በማቅረብ የሴፍቲኔት ፕሮግራም ውስጥ እንዲካተቱ በማድረግ የቀጥታ የኑሮ ማሻሻያ ድጋፍ እንዲያገኙና በቋሚነት ወደ ሥራ ገብተው ራሳቸውን እንዲለውጡ ጥረት እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

አቅም ያላቸው ከስደት ተመላሾች በራሳቸው ወደ ሥራ ለመግባት ጥረት እያደረጉ ሲሆን፤ ከ37ሺህ በላይ የሆኑ ዜጎች ከነቤተሰቦቻቸው የኑሮ ማሻሻያ ድጋፍ እንደተደረገላቸው አስታውቀዋል።

በተጨማሪ የስነ-ልቦናና የአካል ጉዳት ችግር ደርሶባቸው ከፍተኛ ሕክምና የሚያስፈልጋቸው ከስደት ተመላሾች መኖራቸውን ጠቁመው፤ ከገቡበት ችግር ውስጥ በፍጥነት ማገገም እንዲችሉ የተለያዩ የድጋፍና ክትትል ሥራዎች እየተከናወኑ መሆናቸውን አስረድተዋል።

እንደ አቶ ደረጀ ገለጻ፤ ከ160 በላይ የሚሆኑት ከስደት ተመላሾች በቲቢ በሽታ በመጠቃታቸው የተለየ የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል።

እንዲሁም በቆዳና የተለያዩ ተላላፊ በሽታዎች የተጠቁትን በመለየት ወደ ኅብረተሰቡ ሳይቀላቀሉ የሚያገግሙበትን መንገድ ማመቻቸት ተችሏል ብለዋል።

መዳረሻቸውን ደቡብ አፍሪካ በማድረግ ከደቡባዊ የኢትዮጵያ ክፍል የሚነሱና የጂቡቲን መስመር ይዘው መዳረሻቸውን ሳውዲ አረቢያና የመን አድርገው የሚንቀሳቀሱ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ዜጎች መኖራቸውን አመልክተው፤ የስደትን አስከፊነት የሚያስረዱ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች በተለያዩ አካባቢዎች መከናወናቸውን ተናግረዋል።



አቶ ደረጀ ተግይበሉ

በተለይ በሆሳዕና ከተማ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን መሪነት የማኅበረሰብ አንቂዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት አባቶችና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት በተገኙበት ችግሩን ለመፍታት የሚያስችል የንቅናቄና ግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ መካሄዱን አስታውሰዋል።

በዚህም ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ሕገወጥ የሰዎችን ዝውውር ለመከላከል የሚያስችላትን የሆሳዕና አዋጅ እየተባለ የህግ ማዕቀፍ ተግባራዊ ማድረግ መጀመሯን ተናግረው፤ በአካባቢው ይንቀሳቀሱ የነበሩ 153 ሕገወጥ የሰው ዝውውር ላይ የተሳተፉ ሰዎች ከንቅናቄው በኋላ ተይዘው ጉዳያቸው በሕግ እንዲያዝ መደረጉን አስታውቀዋል።

ሕገወጥ የዜጎች ዝውውር ወቅትን ጠብቆ የሚካሄድ ነው፤ አሁን ላይ ሚኒስቴሩ በዚህ ሥራ ላይ ተሳትፎ ያላቸውን ደላሎችን ለሕግ ለማቅረብ ትኩረት አድርጎ እየሠራ ይገኛል ብለዋል።

ከምስራቅ አፍሪካ ከፍተኛ የዜጎች ስደት ያለባት ሀገር ኢትዮጵያ በመሆኗ ችግሩን ለመቀነስ ሁሉም መረባረብ እንዳለበት ገልጸው፤ ሕገወጥ ስደትን ለመቀነስ የውጭ ሀገራት የሥራ ስምሪት አንዱ አማራጭ መሆኑን ጠቁመዋል።

## ከመንገዶች ክፍያ አገልግሎት...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ደወሌ እና ሞጆ - ባቱ በድምሩ አንድ ቢሊዮን 54 ሚሊዮን ብር ገቢ ለማግኘት ታቅዷል ብለዋል።

በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ኢንተርፕራይዙ ከ11 ሚሊዮን በላይ የትራፊክ ፍሰት ማስተናገድ መቻሉን ያነሱት ኃላፊው፤ በመንገድ ላይ የሚደርሰውን ጉዳትና ብልሽት በወቅቱ ጥገና በማድረግ በኩል ክፍተቶች እንደነበሩ አስታውሰዋል።

ክፍተቶቹ የታዩት የግብአት በወቅቱ የመድረስ ችግር በመኖሩ መሆኑን ተናግረው፤ የተወሰኑ ግብአቶች በመግባታቸው ምክንያት በአሁኑ ወቅት የተሻለ የጥገና ወቅታዊነት መኖሩንም አንስተዋል። ይህም የተሽከርካሪዎች ደህንነት እና የመንገድ ላይ አደጋዎችን ለመቀነስ የራሱ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ጠቁመዋል።

በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ከአዲስ አበባ- አዳማ 452 የትራፊክ አደጋ ደርሶ 28 ሞት መድረሱን፣ ድሬዳዋ - ደወሌ 133 የትራፊክ አደጋ ተከስቶ 36 ሞት መመዝገቡንም ተናግረዋል። ሞጆ - ባቱ ደግሞ 186 አደጋ ደርሶ 13 ሞት የተከሰተ ሲሆን በድምሩ 77 ሞት ተመዝግቧል ብለዋል።

ለአደጋ መንስኤ ከሆኑት መካከልም የአሽከርካሪዎች የባህሪ ችግር፣ ከፍጥነት ወሰን በላይ ማሽከርከር፣ የትራፊክ ደንብ መተላለፍ፣ የተሽከርካሪዎች የቴክኒክ አቅም ብቃት ማነስ በዋናነት እንደሚገኙበት አቶ ዐብይ ጠቅሰዋል። ድሬዳዋ- ደወሌ የክፍያ መንገድ ደግሞ ሕገ ወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎች ትርፍ ሰዎች ጭነው ከፍጥነት በላይ በማሽከርከር የሚከሰት አደጋ በዋናነት ከተለዩት ምክንያቶች የሚካተት መሆኑንም አመልክተዋል።

አደጋ ለመቀነስ፤ የፍጥነት ወሰን ቁጥጥር ቴክኖሎጂዎችን ለመተግበር፣ የተጠናከረ የትራፊክ ደንብ ቁጥጥር፣ መሠረታዊ የተሽከርካሪዎች ቴክኒክና ቁጥጥር፣ የመንገድ ኦዲት ቁጥጥር መርሀ ግብር እና የመንገድ ኦዲት ደህንነት ማሻሻያ መርሀ ግብር እንደሚተገበርም አስረድተዋል።

በድሬዳዋ-ደወሌ መስመር ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር በሚያካሂዱ ተሽከርካሪዎች ላይ ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግም ዘንድሮ በልዩ ሁኔታ ለመተግበር ከተለዩት መካከል የሚጠቀሱ ናቸው ብለዋል።

## መንግሥት ከመጠባበቂያ መጋዘኑ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ከመጠባበቂያ የምግብ ክምችት መጋዘን ውስጥ ድጋፍ ማድረጉን ገልጸዋል። ይህን ያደረገው የአሜሪካ ተራድኦ ድርጅትና አጋር አካላት በኢትዮጵያ ለተወሰኑ ወራት ምግብ ነክና ሌሎችንም ሰብዓዊ ድጋፎች ማቋረጣቸውን ተከትሎ እንደሆነም ጠቅሰዋል። አሁንም ቅድሚያ ለሚያስፈልጋቸው አራት ሚሊዮን ዜጎች የምግብ ድጋፍ ለማድረግ ዝግጅት ማድረጉን አስታውቀዋል።

ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ዜጎች የቤት ለቤት ቆጠራን ጨምሮ እርዳታው እንዴትና በምን አግባብ ይድረስ የሚለው የማጣራትና የአኗኗር ሁኔታን የሚያትት የኢኮኖሚ ትንተና ሥራ እየተከናወነ እንዳለ በመጥቀስ፤ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሁለተኛው ዙር ድጋፍ ቅድሚያ ለሚያስፈልጋቸው ዜጎች ተደራሽ እንደሚሆን ተናግረዋል። ለዚህም ከክልል መንግሥታትና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት እየተሠራ ነው ብለዋል።

ሰብዓዊ ድጋፉ በተለያዩ ምክንያት ለተፈናቀሉና በምግብ ችግር የቅድሚያ ቅድሚያ ለሚያስፈልጋቸው ዜጎች ትኩረት በማድረግ የሚሰጥ መሆኑንም ነው አቶ አታለለ የገለጹት። ዝግጅቱ በመጠናቀቅ ላይ እንዳለ በማንሳት፤ አንዳንድ አካባቢዎች ላይ ያለው የፀጥታ ሁኔታ ካልገደበ በስተቀር ድጋፉ እስከ መጪው ሳምንት ለዜጎች እንደሚደርስ ጠቅሰዋል።

ትክክለኛ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ዜጎች የመለየቱ ሥራም ጥናት ላይ የተመሰረተ መሆኑን አንስተው፤ በዚህም የተለያዩ ተቋማት በተለይም የቤት ለቤት ቆጠራና የአኗኗር ሁኔታን የሚያትት የኢኮኖሚ ትንተና ሥራው ላይ ተሳታፊ መሆናቸውን ገልጸዋል።

መንግሥት ከመጠባበቂያ መጋዘኑ በሀገሪቱ በተለያዩ አካባቢዎች አፋጣኝ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው አራት ሚሊዮን ዜጎች የመጀመሪያ ዙር ሰብዓዊ ድጋፍ መስጠቱ ይታወሳል።

# ወቅታዊ

# ‹‹በተያዘው ዓመት መንግስት በለቀቀልን በጀት ልክ የሚመደቡልንን ተማሪዎች እንደቀደመው ጊዜ ተቀብለን እናስተምራለን››

**- ዶክተር ሳሙኤል ክፍሌ**
**የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተጠባባቂ ፕሬዚደንት**

እፀገነት አክሊሉ



**የዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝ መሆን በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በአጭር ጊዜ ውስጥ መዋቅራዊ ሽግግር ለማምጣት እንደሚያስችል የትምህርት ሚኒስቴር በተደጋጋሚ ሲገልጽም ቆይቷል። የዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝ መሆን መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣትና ከሚታወቀው በተሻለና በተለየ መልኩ በአጭር ጊዜ ውስጥ መዋቅራዊ ሽግግር እንዲመጣ ወሳኝነት እንዳለውም ይታሰባል።**

**በዚህም ትምህርት ሚኒስቴር በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ 10 የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎችን ራስ ገዝ ለማድረግ ትልቅ እቅድ ይዟል። በዚህ እቅድ ውስጥ ከተካተቱት መካከልም ፤ ባህርዳር፣ ጎንደር፣ ጅማ፣ ሀዋሳ፣ አርባ ምንጭ እና መቐለ ዩኒቨርስቲዎች ይገኙበታል። ከተቋቋመ ሰባ ሁለተኛ ዓመቱን የያዘው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ በተያዘው በጀት ዓመት የ—ራስ ገዝ“ አስተዳደርን ተግባራዊ በማድረግ የመጀመሪያው ሆኗል ።**

**እኛም ይህንኑ በተመለከተ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተጠባባቂ ፕሬዚዳንት ዶክተር ሳሙኤል ክፍሌ ጋር ቆይታን አድርገናል። መልካም ንባብ።**

**አዲስ ዘመን-ዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝ መሆናቸው ያለውን ፋይዳ እንዴት ይገልጹታል?**

**ዶክተር ሳሙኤል፡-** ዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝ መሆናቸው በርካታ ፋይዳዎች አሉት። ዩኒቨርሲቲዎች ተልዕኮአቸው ላይ ብቻ ትኩረት እንዲያደርጉ፣ ተወዳዳሪና ብቁ ችሎታ ያላቸው ምሩቃንን ለማፍራትና ጥራት ያለው የምርምር ውጤት እንዲሰሩ በማድረጉ በኩልም ራስ ገዝነታቸው ይጠቅማቸዋል ተብሏል።

ዩኒቨርሲቲዎች ችግር የሚያባብሱ ሳይሆን በሰላም መኖርን እና ዴሞክራሲን የሚሰብኩ ተቋማት እንዲሆኑ በተለይ ሀገር በቀል እውቀቶችን በምርምር ማወቅ፣ ለችግሮች የመፍትሄ ሀሳብ ማመንጨት፣ የዓለምንና የሀገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ በመረዳት ቀጣይ አቅጣጫን ለማመላከትም ነጻነትና ራስ ገዝነት እንደሚያስፈልግ ታምኖበታል።

ይህንን ለማረጋገጥ በመንግሥት ቁርጠኝነት ዩኒቨርሲቲዎች ወደ ራስ ገዝነት እንዲሸጋገሩ በተወሰነው መሰረት የተለያዩ እንቅስቃሴዎች መጀመራቸው ይታወቃል። በዚህም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ዩኒቨርሲቲዎችን የራስ ገዝ የማድረግ ረቂቅ አዋጅን መርምሮ እና አጽድቆ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትም አስተላልፏል።

በመሆኑም ዩኒቨርሲቲዎች ራስገዝነት ወይም በሌላ ስሙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተቋማዊ ነጻነት ማለት ተቋማቱ የአስተዳደራዊ፤ የአካዳሚክ፤ የምርመር፤ የሰው ሃብት አስተዳደር፤ የፋይናንስ ጉዳዮቻቸውን ነጻነት ኖሯቸው በዛው ልክ ደግሞ ተጠያቂነትም እንዳለባቸው አውቀው የሚተገብሩበት ስርዓት ነው።

አንድ ተቋም ተቋማዊ ነጻነት ተጎናጽፏል ወይም ራስ ገዝ ሆኗል ብለን ስናስብ በዋናነት ከአካዳሚና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ጋር ተያይዞ ነጻነት ኖሯቸው ይህንንም ከተጠያቂነት ጋር በመያዝ የተሻለና ውጤታማ ስራን እንዲሰሩ የማስቻል ጅምር ነው።

አስተዳደራዊ ነጻነቱ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱ የራሳቸውን አደረጃጀት እና መዋቅር የመዘርጋት ስልጣን ይሰጣቸዋል፤ በዚህ መሰረት ዩኒቨርሲቲዎቹ ከፍተኛ አመራሮቻቸውን ጨምሮ በመዋቅራቸው ውስጥ የሚያስፈልጓቸውን የአመራር እና የአስተዳደር አካላትን በራሳቸው መመደብ እንዲችሉ መንገድ ይከፍትላቸዋል።

በሌላ በኩልም ፋይናንሻል አቅማቸውን በጀታቸውን በአግባቡ የመጠቀም እድል ይፈጥርላቸዋል። ዩኒቨርሲቲዎች አመራሮችን የመሻር፤ የመሾም፤ ሀብት የመፍጠር፤ የውስጥ መመሪያዎችንና አስተዳደራዊ ስርዓቶችን የመዘርጋት ነጻነት ይኖራቸዋል። ከሁሉም በላይ ደግሞ የሰው ኃብታቸውን በአግባቡ ከመጠቀም ብሎም ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች የመቅጠርና ስርዓቱን እንዲሁም ደመወዝና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን የመወሰን አቅም ይፈጥርላቸዋል። በተለይም ለዩኒቨርሲቲው ብሎም ለአገር ይጠቅማል፤ ችግር ፈቺ የምርምር ስራዎችን ይሰራል ብለው ያመኑበትን ባለሙያ በድርድር እስከመቅጠር ድረስ የሚደርስ ነጻነት እንዲኖራቸው ያስችላቸዋል።

> **ወደፊት ግን የአገሪቱን የማለፊያ ነጥብ ያመጡትን ተማሪዎች እናወዳድራለን፤ ተወዳድረው ካለፉት ውስጥ ደግሞ መክፈል የማይችሉትን መንግስት እንዲከፍልላቸው የምንለይበት አሰራርም እንዘረጋለን። ነገር ግን አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን አይቀበልም የሚለው ነገር የማስረዳትና የመረዳት ችግር እንጂ እንዲህ የሚባል አሰራር የለም**

ከተማሪዎች ቅበላ ጀምሮ አስመርቆ እስከማውጣት ድረስ ያለው ሂደት ጤናማ ብሎም በእውቀት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ለማድረግ ተማሪዎችን አወዳድሮ እስከመቀበል ድረስ ያለውን ውሳኔ የማንንም ድጋፍ ሳይጠይቁ የመወሰን አቅም ይፈጥርላቸዋል።

ተቋማት ራስ ገዝ በሆኑ ቁጥር ለሚያስተምሯቸው ተማሪዎች ምን ዓይነት የትምህርት ስርዓት መከተል እንዳለባቸው ገበያውም በሚፈልገው ልክ የመወሰን ከዛም አልፎ የሚያስትምሩበትን ቋንቋም እስከመወሰን ድረስ እድል ይኖራቸዋል።

በነገራችን ላይ ዩኒቨርሲቲዎችን ራስ ገዝ የማድረግ ጅምሩ ቀደም ባለው ጊዜ በእኛም አገር የነበረ ነው። አሁን ባለንበት ዘመን በጣም ትልልቅና ብዙ የምርምር የቴክኖሎጂ ሽግግርን እያደረጉ ያሉ በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂ የሆኑ ዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝ የሆኑ ናቸው። ምክንያቱ ደግሞ የትምህርት ስራ በራሱ ከፍ ያለ ነጻነትን የሚፈልግ ነው። ለምሳሌ ምርምር ሲካሄድ የተለያዩ ግብዓቶች ያስፈልጋሉ፤ ግብዓቶቹ ደግሞ በአስቸኳይ የግዢ ስርዓት መፈጸም ሊኖርባቸው ይችላል። ነገር ግን አሁን ያለው የፋይናንስና የግዢ ስርዓት ይህንን የሚፈቅድ አይደለም ።

በመሆኑም እነዚህ ችግሮች ተቀርፈው ዩኒቨርሲቲዎች ችግር ፈቺ ሊሆኑ የሚችሉት ራሳቸውን ማስተዳደር ሲችሉ ብቻነው። ዛሬ ላይ ቆመን በዓለም አቀፍ ደረጃ ልንጠራቸው የምንችላቸው ስመ ጥር ዩኒቨርሲቲዎችም ራስ ገዝ ናቸው። የውጤታማነታቸው ምስጢርም ይኸው ነው።

ለምሳሌ እነ ሀርቫርድን ጨምሮ የስቴት ዩኒቨርሲቲዎች የመንግስት ናቸው። ግን ደግሞ ራስ ገዝ አስተዳደርን ስለሚከተሉ በዩኒቨርሲቲዎች ደረጃ ላይ ሁሌም ከላይ የሚታዩ ናቸው። በመሆኑም ራስ ገዝ ማድረግ የዓለም ተሞክሮም እንደሚያሳየው በትምህርት ጥራት፣ በምርምር ስራዎች ላይ የራሱ የሆነ አወንታዊ ሚና እንዳለው ነው።

በኢትዮጵያ ባለፉት ሁለት አስርተ ዓመታት በትምህርት ተደራሽነት ላይ ከፍ ያለ ስራ ተሰርቷል፤ አሁን በመንግስት ደረጃ 51 እና በግል 5 ዩኒቨርስቲዎች አሉ። እንዲሁም 325 አካባቢ የግል ኮሌጆችም ይገኛሉ። በመሆኑም ይህ ተደራሽነት ጥሩ ቢሆንም የዛሬ አምስት ዓመት የትምህርት ፍኖተ ካርታ ጥናት ሲካሄድ የተገኘው ውጤት የሚያሳየው ተደራሽነቱ አበረታች ቢሆንም የትምህርት ጥራቱ ላይ ግን ችግር እንዳለ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘም ምን መሰራት አለበት ለሚለው ፍኖተ ካርታው ካስቀመጠው ምክረ ሃሳብ አንዱ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ራስ ገዝ ማድረግ ነው።

በመሆኑም የዚህን የጥናት ውጤት በመያዝ ዩኒቨርሲቲዎቹ ራስ ገዝ የሚሆኑበትን አሰራር የማመቻቸት ሂደት ነው የተጀመረው። ራስ ገዝ የመሆን ጉዳይም ከጥናቱ ጋር አብሮ የመጣ ጉዳይ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል።

የዓለም ተሞክሮ የሚያሳየንም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ነጻነት ለአካዳሚክ ውጤታማነት ጉልህ ሚና እንዳለው ነው። ሌላውና የሚገርመው ነገር ራስ ገዝ በአገራችን ዛሬ የተጀመረ አሰራር አይደለም፤ በንጉሱ ጊዜ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዩኒቨርሲቲ ሲቋቋም ራስ ገዝ ሆኖ ነው የተቋቋመው፤ በዛን ወቅት የነበረውን ተሞክሮም መለስ ብለን ስናየው በትምህርት ጥራት ላይ የነበረው ሚና ቀላል የሚባል አልነበረም፤ ሆኖም ከመንግስት ለውጥ ጋር በተያያዘ በዛ መልኩ መቀጠል ባለመቻሉ አሁን የደረስንበት ደረጃ ላይ ደርሰናል። በጠቅላላው ግን ራስ ገዝ አንዱ የትምህርት ሚኒስቴር የሪፎርም ስራ አካል ነው።

ከራስ ገዝነት በተጓዳኝ ጥናቱን መሰረት በማድረግ ዩኒቨርሲቲዎችን በሚና የመከፋፈል ስራ ይሰራል። አሁን ላይ ዩኒቨርሲቲዎቻችን በሙሉ የሚሰጡት ትምህርትም ሆነ ደረጃቸው ተመሳሳይ ነው ነገር ግን አንድ ዓይነት መሆን አይጠበቅባቸውም። ስለዚህ ዩኒቨርሲቲዎቹ በትኩረትና በተልዕኮ ሊለያዩ ይገባል ይህም ሲባል

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

# ወቅታዊ

## ‹‹በተያዘው ዓመት መንግስት በለቀቀልን በጀት ልክ...

ከገጽ 7 የዞረ



የተወሰኑት ምርምር ሌሎቹ አፕላይድ ሳይንስ የተቀሩት ሕክምና ከዚህ የሚተርፉት ደግሞ የመማር ማስተማር ስራውን ከምርምሩ ጋር አዋህደው ይቀጥሉ ተብሎ ዩኒቨርሲቲዎቹን የመለየት እንዲሁም ካላቸው አካባቢያዊ ሁኔታና ጸጋ እንዲሁም ከኋላ ታሪካቸው በመነሳት ትኩረት እንዲያገኙ ሆኗል። በዚህ መነሻነትም ከዚህ በኋላ ሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች ተመሳሳይ ስራን አይሰሩም።

**አዲስ ዘመን፡- ትምህርት ሚኒስቴር በተለይም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ የጀመረው የሪፎርም ስራ ምን ዓይነት ውጤቶች የሚጠበቁበት ነው?**

**ዶክተር ሳሙኤል ፡-** ትምህርት ሚኒስቴር በተለይም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ የጀመረው ሪፎርም በደንብ ተጠንቶ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብም ባለቤት ሆኖበት የተሰራ ነው። በተለይም አሁን ላይ የሪፎርም ስራውን ጨርሶ ራስ ገዝ የሆነው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እንደ አነሳሱ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ እስከ መጨረሻው ተሳትፎውን ካደረገበት ተቋሙ ብቁ ሆኖ የማይወጣበት አንዳችም ምክንያት አይታየኝም።

ይህም ማለት ዩኒቨርሲቲው ከዚህ ቀደም የነበረውንም ተሞክሮ ቀምሮ ሪፎርሙንና ራስገዝ የመሆን እድሉን ተጠቅሞ ብቁ ተማሪዎችን ማፍራት የሚችል፣ የተሻሉና የአገርን የህዝብን ችግር ሊፈቱ የሚችሉ ምርምሮችን ማካሄድ የሚችል፣ ለአገር መፍትሔ ማምጣት የሚችሉ ሀሳቦች የሚፈልቁበት ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ ለአገራችን የዲፕሎማሲ አቅም ሊሆን የሚችል ተቋም ይሆናል። በሌላ በኩልም በሀብት አጠቃቀም ማመንጨትና አያያዝ በኩልም ለሌሎች መሰል ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት አርዓያ መሆን የሚችል ተቋም እንዲሆን ያስችለዋል። ሪፎርሙም በዋናነት የሚያሳካው ይህንን ነው።

ብቁ ተቋማት አገር ያስቀጥላሉ እንዲሁም የወደፊቱን ጊዜ መሸከም ይችላሉ፤ በመሆኑም ትምህርት ሚኒስቴር በዩኒቨርሲቲው ላይ ሲሰራ የቆየውም ሪፎርም ይህንን የሚያመጣ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- አንድ ተቋም ተቋማዊ ነጻነት ተጎናጽፏል ወይም ራስ ገዝ ሆኗል ብለን ስናስብ በዋናነት ከአካዳሚና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ጋር ተያይዞ ነጻነት ኖረው ማለት እንደሆነ እንረዳለን አሁን ደግሞ ቻንስለሩን ጨምሮ እርሶም ተጠባባቂ ፕሬዚዳንት የሆኑት በሹመት ነውና እነዚህ ሀሳቦች አይጣረሱም?**

**ዶክተር ሳሙኤል፡-** ዩኒቨርሲቲዎቹ የህዝብ ናቸው፤ ሕዝብ ደግሞ እንዲያስተዳድረው የወከለው መንግስት አለ፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ ዩኒቨርሲቲዎቹ እንዴት መመራት አለባቸው የሚለውን የሚገዛ የወጣ ሕግም አለ።

በሌላ በኩል ደግሞ ዩኒቨርሲቲው ራስገዝ ሲሆን ቻንስለር ይኖረዋል ይላል ሕጉ በሌሎች አገራት ያለው ተሞክሮ እንደውም ዩኒቨርሲቲው ያለበት ከተማ ከንቲባ ወይም የክልሉ ገዥ ነው ቻንስለር የሚሆነው፤ እኛም የሄድነው በዚሁ መሰረት ነው። ዞሮ ዞሮ ራስ ገዝ ሆነው በራሳቸው የሚንቀሳቀሱ ዩኒቨርሲቲዎች በየትኛውም ዓለም የሚሰራው በዚህ መሰረት ነው።

ተጠባባቂ ፕሬዚዳንትነትንም በተመለከተ መጀመሪያም ቢሆን ተጠባባቂ ያስፈለገበትም ሆነ፤ ለሆነ አካል ተጠባባቂነት የተሰጠበትም የራሱ ምክንያቶች አሉት፤ ሪፎርሙ ሁለት ዓመቱን ያሳለፈው እንደ ሽግግር ጊዜ ነበር። ለመጀመሪያ ጊዜ ራስ ገዝ ሆኖ ለተቋቋመው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንትም ሆነ ቻንስለር መሾም አስፈላጊ በመሆኑ ብዙ አውጥተን ሰዎችን ሾመናል። ሹመቱም ከውጭ አዲስ ሰው ቢመጣ ይሻላል አይሻልም፤ ያሉት ሰዎች ቢቀጥሉ ይሻላል ወይስ ስራውን በቅርበት እንደ እኔ ሲከታተሉ የነበሩ ሰዎችን ቢመደቡ ይሻላል የሚለው ሁሉ ታይቶ ነው የተወሰነው።

ሪፎርሙን መሬት አስነክቶ ራስ ገዙ የመፍጠር ሁኔታ መስመር ይዞ በውድድር ፕሬዚዳንቶችና ምክትል ፕሬዚዳንቶች ተመርጠው በአዲሱ መዋቅር ዩኒቨርሲቲው ስራውን እንዲቀጥል ያደርጋል አያደርግም የሚለው ሁሉ ታይቶ ነው ወደ ውሳኔ የተገባው።

እኔ በበኩሌ ሪፎርሙ እንዴት መሬት መያዝ እንዳለበት የሚሰራውን ስራና የሽግግሩን ጊዜ እንድመራ እንጂ በቋሚነት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት እንድሆን አይደለም። ይህንን ስናደርግ ዩኒቨርሲቲው ራስገዝነቱን የሚሸራርፍ ነገር በተለየ ሁኔታ እንዲታይ የሚያደርገውን ነገር ለማስቀረት ካለን ፍላጎት የተነሳ ነው ይህንን ያደረግነው።

በዚህ መልኩ ከሄድን በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሪፎርሙ የሚፈልጋቸውን ርምጃዎች (ሂደቶች ) ሄደን አዲስ አመራር አስመርጠን ዩኒቨርሲቲው ራሱን የቻለ ገለልተኛ ራስገዝ ዩኒቨርሲቲ አስደርገን ኃላፊነታችንን እንጨርሳለን።

**አዲስ ዘመን፡- ተማሪዎች ተወዳድረውና ከፍለው ይማሩ መባሉ የትምህርት አቅሙ ቢኖራቸውም ከፍለው ለመማር ግን አቅም የሌላቸውን የሕብረተሰብ ክፍሎች ይጎዳል እንደውም ፍትሃዊነትም ላይ ከፍ ያለ ችግር ያስከትላል እየተባለ ነውና እርስዎ በዚህ ላይ ምን ይላሉ?**

**ዶክተር ሳሙኤል፡-** ይህ ነገሩን በትክክል ከማስረዳትና ከመረዳት ማነስ የመጣ ውዥንብር አድርጌ ነው የምወስደው:: ነገር ግን አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም ይሁን ሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች በአጠቃላይ ያለፈን ተማሪ በሙሉ ሲቀበሉ አልኖሩም:: ሁሌም ቢሆን ተማሪዎች በየዩኒቨርሲቲው የሚመደቡት በውድድር ነው። መንግስት ዩኒቨርሲቲዎችን ራስገዝ ሲያደርግ ደግሞ አሰራሩ ሁለት መልክ ይኖረዋል፤ በዚህም መንግስት በጀት መድቦላቸው የሚማሩ ተማሪዎች አሉ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ዩኒቨርሲቲው የሚጠይቀውን ክፍያ አሟልተው የሚማሩ ይኖራሉ፤ ተማሪዎችን ከትምህርት ሚኒስቴር (መንግስት) አልቀበልም ማለት በጀትም አልፈልግም እንደማለት ነው፤ በመሆኑም በአንድ በኩል ለመደበኛ ስራ ማስኬጂያችን በጀት እየጠየቅን በሌላ ጎን ደግሞ ተማሪ አትመድቡብን ማለት አንችልም።

ነገር ግን ይህም ቢሆን ዩኒቨርሲቲው ራስገዝ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በተሰጠው ነጻነት መሰረት የመክፈል አቅም ያላቸውን ተማሪዎች አወዳድሮ መቀበል ይችላል። በያዝነው 2016 ዓ.ም ተማሪዎች ከትምህርት ሚኒስቴር (ከመንግስት) ይመደባሉ፤ ምናልባትም አሁን በጀመርነው ፍጥነት ስራው በትክክል የሚሄድ ከሆነ በሁለተኛው መንፈቅ ዓመት ከፍለው መማር የሚችሉ የተወሰኑ ተማሪዎችን በጥቂት ፕሮግራሞች ላይ ለመቀበል እንሞክራለን።

እዚህ ላይ ሁሉም ሊያውቀው የሚገባው ነገር በተያዘው ዓመት መንግስት በለቀቀልን በጀት ልክ የሚመደቡልንን ተማሪዎች እንደቀደመው ጊዜ ተቀብለን እናስተምራለን።

ወደፊት ግን የአገሪቱን የማለፊያ ነጥብ ያመጡትን ተማሪዎች እናወዳድራለን፤ ተወዳድረው ካለፉት ውስጥ ደግሞ መክፈል የማይችሉትን መንግስት እንዲከፍልላቸው የምንለይበት አሰራርም እንዘረጋለን። ነገር ግን አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን አይቀበልም የሚለው ነገር የማስረዳትና የመረዳት ችግር እንጂ እንዲህ የሚባል አሰራር የለም። ራስገዝ በሚል እሳቤ ፍትሃዊነትንም ማዛባት አይቻልም። የመንግስት ተቋም መሆኑም አይቀርም። እዚህ ላይ ግን የመንግስት ተቋም ሆኖ ጠንካራ ተወዳዳሪ ብቁ ባለሙያዎችን የሚያስመርቅ ተቋም እንዲሆን እንፈልጋለንም፤ እንሰራለንም። የተማሪዎችን አቀባበልና ወጪ አሸፋፈን በተመለከተም ከምንፈልገው ጉዳይ ውስጥ አንዷት ነጠላ ጉዳይ ከመሆኗም በላይ የሪፎርሙ ስራ ወይም የሚጠበቀውም ውጤት ይኸው ብቻ አይደለም።

**አዲስ ዘመን፡- አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ራስገዝ ከመሆኑ ጋር በተገናኘ ከሌሎች ዓለም አቀፍ ራስገዝ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር የሚኖረው ግንኙነት ምን ዓይነት መልክ እንዲኖረው ነው የሚፈለገው?**

**ዶክተር ሳሙኤል፡-** በነባሩም የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ የመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ከውጭ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር የመስራት ነጻነት አላቸው። ይህ ራስገዝነታቸው የሚሰጣቸው ሳይሆን ተፈጥሯዊ የአሰራር ሂደታቸው ነው። በዓለም ዙሪያ ካሉ ተመሳሳይ የትምህርት ተቋማት ጋር የመግባቢያ ሰነድ የመፈራረም፤ ውል የመዋዋል፤ በጋራ ተማሪ የማስተማርና ምርምሮችን የመስራት በጋራ መምህራንን የማልማት ጉዳይ ላይ ይሰራሉ።

ይህ የቆየው የአሰራር ሂደታቸው ደግሞ ራስገዝ በመሆን በሚጎናጸፉት ነጻነት ይበልጥ ይጠናከራል እንጂ እንደ አዲስ የሚሰራ ወይም የሚኬድበት ጉዳይ አይሆንም። ጠንካራ ዓለም አቀፍ ግንኙነት እንዲኖረን ደግሞ እስከ አሁን ያልሰራንበት ከእኛ የጎደለ ነገር ካለ ፈትሸን የምናጠናክረው ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- ዩኒቨርሲቲው ራስገዝ በመሆኑ በተለይም የተማረ የሰው ኃይል ፍልሰትን ሊያስቀረው፤ ማስቀረት እንኳን ባይችል ይቀንሰዋል ብለው ያስባሉ?**

**ዶክተር ሳሙኤል፡-** ሰዎች ተምረው በእውቀታቸው አገራቸውን ማገልገል ሲገባቸው ለምን አገር ጥለው ይሄዳሉ የሚለው ነገር ኢኮኖሚያዊ አልያም ፖለቲካዊ ችግር ብቻ አድርገን መውሰድ ይከብዳል፤ በርካታ ጉዳዮችም አሉ፤ ዋናው ግን የግል ውሳኔ ነው። እንደ እኛ ግን በዓለም ዙሪያ ያሉ ኢትዮጵያውያን ለሳምንትም ለአንድ መንፈቅም መጥተው ዜጎቻቸውን በአንድ ወይም በሌላ መንገድ የተማሩባቸውን የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎችን ቢደግፉ ደስታችን ነው። ለዚህ ሊያበቁ የሚችሉ በእኛ በኩል መሰራት ያለባቸውን ስራዎች እንሰራለን።

በሌላ በኩል ደግሞ እጃችን ላይ ያሉ ምሁራኖቻችን የተሻለና ምቹ የስራ አካባቢ እንዲፈጠርላቸው በዚህ ሪፎርም ውስጥ ሆነን እንሰራለን። የስራ ቦታቸው፤ የሚያገኙት ክፍያ፤ በየጊዜው ሊኖራቸው የሚገባው የስራ እድገት፤ ሊያገኙት የሚገባውን ያህል እውቅና ከሰጠናቸውና እነዚህን ነገሮች ካስተካከልንላቸው በአገራቸው ላይ ለመኖር፤ ለመስራት፤ አገራቸውንም ራሳቸውንም ለመለወጥ ሌላ ምክንያት አይፈልጉም ብዬ አምናለሁ፤ በመሆኑም አሁን የምንከተለው አቅጣጫ እጃችን ላይ ያሉትን ማቆየት ነው።

በዓለም ዙሪያ ያሉ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሆኑ ምሁራንን ደግሞ ወደአገራቸው ወደመሰረታቸው ተመልሰው አገር እንዲያገለግሉ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲንም እንዲያገለግሉ በዛ ውስጥ ደግሞ ለአገርና ለህዝብ አስተዋጽዖ እንዲያደርጉ የበኩላችንን እናደርጋለን።

**አዲስ ዘመን፡- አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እንደ ማሳያም የራስ ገዝነት ጉዞውን አንድ ብሎ ጀምሯልና ይህ አካሄድ እንደው ከጊዜ ወደጊዜ እየወደቀ መጣ ለሚባለው የትምህርት ጥራት የሚኖረው አስተዋጽኦ እንዴት ይገለጻል?**

**ዶክተር ሳሙኤል፡-** የተማሪ ቅበላ ስርዓቱ በውድድርና ጠንካራ ይሆናል፤ የመግቢያ መስፈርቱም ብቃትን መሰረት ያደረገ ይሆናል። ከአመራር ጀምሮ እስከ ተማሪዎች ድረስም ብቃት ይታያል ማለት ነው። ማንኛውም መምህር በሂደት ራሱን ካላበቃና ካላሳደገ ዘላለሙን መምህር ሆኖ የሚቆይበት እድል የጠበበ ነው የሚሆነው።

በሁለትና በሶስት ዓመት ውለታው ሲታደስ ብቃትን መሰረት አድርጎ ከመሆኑም በላይ ይህ መምህር ባለፈው ኮንትራቱ ከታደሰለት በኋላ በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ ምን አስተዋጽዖ አበርክቷል?፤ ምርምር ላይ የነበረው ስራ ምን ይመስላል? ምን ያህል ጥናቶችን ለህትመት አብቅቷል ? ሀብት በማምጣት በኩልስ ሚናው ምን ነበር? ለማህበረሰቡ የሚጠቅም ነገር ላይ ምን አድርጓል? ተቋምን በመደገፍና በመምራት በኩል አስተዋጽዖው እንዴት ይለካል ? ውለታውን ማደስ ይገባል አይገባም የሚል ታይቶ የሚወሰን ይሆናል።

ይህ አሰራር ደግሞ ሌላው ዓለምም የሚጠቀምበት ነው። ወደእኛ አገርም አምጥተን ከነባራዊ ሁኔታዎቻችን አንጻር ቃኝተነው የምንተገብረው ይሆናል።

ውድድር ሲመጣም ብቃትን መሰረት ያደርጋል። ብቃት የሌላቸውንም ቀስ እያልን ከስርዓቱ የምናስወጣበትና በብቃትና በፍትህ ላይ የተመሰረተ የእውቅና ስርዓት እንዲዘረጋ ደግሞ እናደርጋለን።

**አዲስ ዘመን፡- እንደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በትምህርት ክፍሎችስ ላይ ለውጦች ይኖሩ ይሆን?**

**ዶክተር ሳሙኤል፡-** እስከ አሁን በዚህ ዙሪያ የሰራነው ስራም የለም፤ ውይይትም አልጀመርንም። ወደፊት ግን በዝርዝር ፈትሸነው ለውጥ የሚኖር ከሆነ ለውጡም ለዩኒቨርሲቲው ጠቃሚ መስሎ ከታየን እንሄድበታለን። ነገር ግን ለውጥ መጣ ለማስባል ብቻ የሆኑ የትምህርት ክፍሎችን በማጠፍና በመዘጋት አላምንም።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በጣም አመሰግናለሁ።**

**ዶክተር ሳሙኤል፡-** እኔም አመሰግናለሁ

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## የ ‹‹ብሪክስ›› አባልነት - ለኢንቨስትመንት ዘርፍ እድገት

**አንተነህ ቸሬ**

ከዓለም የቆዳ ስፋት 27 በመቶ በሚሸፍኑት፣ ከዓለም ሕዝብ የ42 በመቶው ባለቤት በሆኑት፣ ለጠቅላላው የዓለም ምርት 27 በመቶ ያህሉን በሚያበረክቱት እንዲሁም በፈጣን የምጣኔ ሀብት እድገት ላይ ከሚገኙ የዓለም ሀገራት መካከል ግንባር ቀደሞች በሆኑት ብራዚል፣ ሩስያ፣ ሕንድ፣ ቻይናና ደቡብ አፍሪካ ጥምረት የተመሠረተው ‹ብሪክስ› (BRICS) አባል ሀገሮች የገቢ ንግድ ከፍተኛ መሆኑንም መረጃዎች ያመለክታሉ።

መረጃዎቹ እንዳሉት፤ የአባል ሀገሮቹ በዓለም ላይ ያሉ ሸቀጦችን ወደ ሀገራቸው በማስገባት ረገድ 14 በመቶ ጥቅል ድርሻ አላቸው፤ የቻይናን የገቢ ንግድ ብቻ ብንመለከት እስከ ሁለት ትሪሊዮን ዶላር ሲደርስ፣ በጥቅሉ አምስቱ ሀገሮች ብቻ 3 ነጥብ 6 ትሪሊዮን ዶላር የገቢ ንግድ ልውውጥ አላቸው።

ቡድን 7 በመባል የተሰባሰቡት ሀብታምና ሃያላን ሀገሮች የጋራ ሀብት እዚህ ሀብት ላይ አይደርስም፤ የብሪክስ ስብስብ ሀገሮች ከቡድን 7 ሀገሮች በላይ በፍጥነት እያደጉ ያሉ፣ በቀጣይም ለማደግ ሰፊ ተስፋ ያላቸው ሀገሮች ናቸው፤ ቻይናና ህንድን የመሳሰሉት ሀገሮች ደግሞ የበለጠ ለማደግ ምቹ ሁኔታና ተስፋ እንዳላቸውም መረጃዎቹ ይጠቁማሉ።

ጥምረቱ አጀማመሩ ምጣኔ ሀብታዊ ዓላማዎች ላይ ያተኮረ ነበር። ይህ ጥምረት ቀስ በቀስ የተደራጀ ዓለም አቀፋዊ የጂኦፖለቲካ ቅርፅና መዋቅር ይዞ፣ ዛሬ የ‹‹ቡድን ሰባት›› (G7) አቻ ተፎካካሪ ሆኖ እየተጠቀሰ ነው። የጥምረቱ አባላት ያቋቋሙት ‹‹ኒው ዴቨሎፕመንት ባንክ›› (New Development Bank) የምዕራባውያን፣ በተለይም የአሜሪካ፣ ተፅዕኖ ጎልቶ የሚታይባቸውን ነባሮቹን የፋይናንስ ተቋማት (የዓለም ባንክ እና የዓለም የገንዘብ ድርጅት) ያላቸውን አይነት ኃላፊነት እንደተሰጠውም ይገለፃል።

በአሜሪካ የሚመራው የምዕራቡ ዓለም የኃያላን መንግሥታት ኅብረት ተገዳዳሪ ለመሆን እየጣረ እንደሚገኝ የሚነገርለት ይህ ጥምረት፣ የበርካታ ሀገራትን ቀልብ መሳብ ችሎ ከ40 በላይ ሀገራት የጥምረቱ አባል ለመሆን ፍላጎታቸውን አሳይተዋል። ጥምረቱ ባለፈው ነሐሴ ወር 2015 ዓ.ም፣ በጆሃንስበርግ (ደቡብ አፍሪካ) ባካሄደው 15ኛው ዓመታዊ ጉባዔው፣ የአባልነት ጥያቄ ካቀረቡ ሀገራት መካከል የስድስቱን (ኢትዮጵያ፣ የተባበሩት አረብ ኤምሬቶች፣ ኢራን፣ ግብጽ፣ ሳውዲ አረቢያ እና አርጀንቲና) የአባልነት ጥያቄ ተቀብሏል።

ከአዳዲሶቹ የ‹ብሪክስ› አባላት መካከል አንዷ የሆነችው ኢትዮጵያ፣ አባልነቷ በምጣኔ ሀብታዊና ዲፕሎማሲያዊ መስኮች ያስመዘገበቻቸው ስኬቶች ውጤት እንደሆነና ይህ አባልነትም በቀጣይ ጊዜያት በምጣኔ ሀብትና በፖለቲካ መስኮች ዘርፈ ብዙ ጥቅሞችን እንደሚያስገኝላት ተገልጿል።

ኢትዮጵያ የጥምረቱ አባል መሆኗን ተከትሎ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ዶ/ር ባስተላለፉት መልዕክት ‹‹ብሪክስ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዓለም ካሉ ስብስብ ኃይሎች መካከል በህዝብ ብዛት፣ በኢኮኖሚና በመደመጥ አቅሙ እያደገ የመጣ ቡድን ነው። ይህ ቡድን እያደገ ከመጣ በኋላ፣ ከ40 የማያንሱ ሀገራት ‹ብሪክስ›ን ለመቀላቀል ፍላጎት አሳይተዋል፤ ከእነዚህ ሀገራት መካከል አሁን ስድስት ሀገራት መመዘኛውን አሟልተው የብሪክስ አባል መሆን ችለዋል። ይህ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ብሎም ለአፍሪካ ትልቅ ኩራትና ዲፕሎማሲዊ ድል ነው።›› ሲሉ ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ ለአባልነት ስትመረጥ ታሪኳ፣ የሕዝብ ብዛቷ፣ በተለይ በአሁኑ ወቅት በዓለም ላይ ከፍተኛ እድገት እያስመዘገቡ ከሚገኙ ጥቂት ሀገራት መካከል አንዷ መሆኗ ስለታመነበት መሆኑን ጠቅሰው፣ ኢትዮጵያ ውስጥ እየተካሄደ ያለው አረንጓዴ ዐሻራ፣ በግብርና ራስን ለመቻል እየተደረገ ያለው ጥረት እና የመደመጥ አቅሟ እያደገ መምጣትም ‹ኢትዮጵያን አባል ማድረግ የደቡብ-ደቡብ ትብብርን (South-South Cooperation) እውን ለማድረግ እንደሚያስችል፣ ኢትዮጵያ በሌለችበት ትብብሩ ሊሳካ አይችልም በሚል ታምኖበት መሆኑንም ገልጸዋል።

**የጥምረቱ አባላት ከአጠቃላይ የዓለም ሕዝብ ቁጥርም ሆነ ምጣኔ ሀብት ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው መሆናቸው ትልቅ የገበያ ባለቤት ያደርጋቸዋል፡፡ ይህ የትልቅ ገበያ ባለቤትነት አማራጭ የገበያ እድሎችን በማስፋት ለምጣኔ ሀብት እድገት ትልቅ አስተዋፅኦ ያበረክታል**

‹‹ከሁሉም ጋር ባካሄድነው ንግግር የኢትዮጵያ የ‹ብሪክስ› አባል መሆን ለአፍሪካም ሆነ ለየደቡብ-ደቡብ ትብብር ወሳኝ መሆኑን አምነዋል›› ሲሉም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተናግረዋል። አሁን እየተመዘገበ ያለውን ለውጥና ድል ዓለም በደንብ ተገንዝቦት እውቅና እየሰጠው እንደሚገኝም ጠቅሰው፣ ይህ ለኢትዮጵያም ትልቅ ድል መሆኑን አስታውቀዋል።

‹‹ዝም ብሎ መግባት ሳይሆን በእያንዳንዱ መስፈርት በኢኮኖሚ እድገት፣ በሕዝብ ቁጥር፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ በመደመጥ አቅማችንና ወደፊት ባለን ተስፋ ምክንያት ‹በአፍሪካ ትልቅ ተደማጭነት ያላት ሀገር በመሆኗ ኢትዮጵያን ጥለን አፍሪካን አካተትን ማለት አንችልም› የሚል ድምዳሜ ላይ ተደርሶ ነው ጥምረቱን የተቀላቀልነው። ጥምረቱን መቀላቀላችን ብቻም ሳይሆን በጥምረቱ ውስጥ ያለን ተደማጭነትና ግንኙነት ጠንካራ እንዲሆን አድርጓል። ይህ በጣም ትልቅ ድል ነው›› ሲሉ ገልጸዋል።

ሀገሪቱ ባልገባችባቸውና መግባት ባለባት መድረኮች ላይ ሁሉ እየተሳተፈች ድምጿን ከሀገሯ በላይ በአህጉርና በዓለም ደረጃ የምታስደምጥ ሀገር እንደምትሆንም አመልክተዋል። በስንዴ ምርት፣ በአረንጓዴ ዐሻራ፣ በከተሜነት፣ በአጠቃላይ በሀገራዊ ምርት ያስመዘገበቻቸውን ድሎች በዲፕሎማሲውም እየደገመች መሆኗን አስታውቀው፣ ‹‹ይህንንም አጠናክረን እንቀጥላለን›› ብለዋል።

ኢትዮጵያ የ‹ብሪክስ‹ አባልነት ጥያቄዋ ተቀባይነት ማግኘቱ ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ፣ በተለይም የኢንቨስትመንት፣ ዘርፍ አዎንታዊ ሚና እንደሚኖረው የምጣኔ ሀብት ጥናት ምሁራን ይገልፃሉ። በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ መምህር እና በኢባዳን ዩኒቨርሲቲ የዶክትሬት ዲግሪ ተማሪ የሆኑት ረዳት ፕሮፌሰር ሀብታሙ ግርማ፣ ኢትዮጵያ የ ‹ብሪክስ› አባል እንድትሆን መወሰኑ፣ ተጨማሪ የፋይናንስ አቅርቦት እና የገበያ እድል በመፍጠር የኢንቨስትመንት ዘርፉን ለማጠናከር ትልቅ እገዛ እንደሚያደርግ ይገልፃሉ።

እርሳቸው እንደሚሉት፣ የ‹ብሪክስ› የኢንቨስትመንት ዘርፍ የትኩረት መስኮች ከኢትዮጵያ የዘርፉ የትኩረት መስኮች ጋር የሚጣጣሙ በመሆናቸው አባልነቱ ለሀገሪቱ የኢንቨስትመንት ዘርፍ በጎ አስተዋፅኦ ይኖረዋል። የ‹ብሪክስ› አባል መሆን የኢንቨስትመንት ፋይናንስ የዚህ አደረጃጀት አባል መሆን የፋይናንስ ተጠቃሚ ያደርጋል። አባል ሀገራቱ ያቋቋሙት ባንክ (New Development Bank) ሀገራቱ የሚገጥማቸውን የፋይናንስና የውጭ ምንዛሬ እጥረት የማቃለል ዓላማ ያለው በመሆኑ፣ ለኢንቨስተሮች ተጨማሪ የፋይናንስና የውጭ ምንዛሬ ምንጭ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል። የኢንቨስትመንት ፈንድ ለማግኘት ይረዳል። ለአስቸኳይ የፋይናንስ ችግሮች መፍትሄ ይሆናል። ይሁን እንጂ ባንኩ ትልቅ የኢንቨስትመንት ባንክ ሆኖ አስተማማኝ የፋይናንስ ምንጭ ለመሆን ብዙ መሥራት እንደሚጠበቅበትም ይጠቁማሉ።

‹ብሪክስ› ከኢንቨስትመንት ሚናው በተጨማሪ በአንዳንድ የውጭ ሃይሎች የሚደርሱ አሻጥሮችን ለማስታገስና ለመቀነስ ትልቅ አስተዋፅዖ እንደሚኖረውም ረዳት ፕሮፌሰር ሀብታሙ ይናገራሉ። ‹‹ባለፉት ጥቂት ዓመታት ኢትዮጵያ ትልቅ የኢኮኖሚና የፖለቲካ አሻጥሮች ሲፈፀሙባት እንደነበር ይታወሳል። የምዕራቡ ዓለም ጣልቃ ገብነት አንዱ መገለጫ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ማዳከም ነው። ጥምረቱ በውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ዘርፍ ያለውን አሻጥር (የውጭ ምንዛሬና የገበያ ክልከላዎችን…) ለመቀነስ ይረዳል። ባለፉት ሦስት ዓመታት ኢትዮጵያ ከፍተኛ የውጭ ጫና ባጋጠማት ጊዜ የ‹ብሪክስ› አባል ብትሆን ኖሮ ብዙ ጫናዎች ይቃለሉላት ነበር›› ይላሉ።

የ‹ብሪክስ› አባልነት የኢንቨስትመንት ፋይናንስ ለማግኘት ከሚያደርገው እገዛ ባሻገር፣ የገበያ አማራጭን በማስፋት ረገድም አዎንታዊ ሚና እንደሚኖረው ረዳት ፕሮፌሰር ሀብታሙ ያስረዳሉ። የጥምረቱ አባላት ከአጠቃላይ የዓለም ሕዝብ ቁጥርም ሆነ ምጣኔ ሀብት ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው መሆናቸው ትልቅ የገበያ ባለቤት ያደርጋቸዋል። ይህ የትልቅ ገበያ ባለቤትነት አማራጭ የገበያ እድሎችን በማስፋት ለምጣኔ ሀብት እድገት ትልቅ አስተዋፅኦ ያበረክታል። የውጭ ባለሀብቶች በኢንቨስትመንት ለመሰማራት ግምት ውስጥ ከሚያስገቧቸው መስፈርቶች መካከል አንዱ የገበያ እድል (Market Availability) ነው። አምራቾች ሰፊ ገበያና ከፖለቲካ ጫና ነፃ የሆነ የቢዝነስ ከባቢ ይፈልጋሉ፤ ‹ብሪክስ› እነዚህን እድሎች ስለሚያመቻች የጥምረቱ አባል መሆን ኢንቨስተሮች ወደ ሥራ እንዲሰማሩ ያበረታታቸዋል።

‹‹የ ‹ብሪክስ› ባንክ የኢንቨስትመንት ፋይናንስ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል። የኢንቨስትመንት ማደግ የምርት መጠንን ያሳድጋል፤ የምርት ማደግ ደግሞ የገበያ እድልን ያሰፋል። ባንኩ የሚፈጥረው የኢንቨስትመንት ፋይናንስ አቅርቦት እድል እና የጥምረቱ አባል ሀገራት የገበያ አቅም ተመጋጋቢ ናቸው›› ይላሉ።

በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ መምህርና በ ‹‹ፍሮንቲየርአይ (Frontieri)›› ጥናትና አማካሪ ድርጅት ከፍተኛ ተመራማሪ የሆኑት ዶክተር ሞላ አለማየሁ በበኩላቸው፣ የ ‹ብሪክስ› አባል መሆን ምጣኔ ሀብታዊ ጥቅሞችን የሚያስገኝ ቢሆንም ሊያስከትለው ስለሚችለው ጉዳትም በጥልቀትና በጥንቃቄ ማሰብ እንደሚገባ ይመክራሉ። እንደርሳቸው ማብራሪያ፣ የ ‹ብሪክስ› አባልነት አዳዲስ የኢንቨስትመንትና የገበያ አማራጮችን እንዲሁም በመስፈርቶች ያልተገደበ ብድር ለማግኘት ሰፊ እድል የሚፈጥር ቢሆንም፣ የጥምረቱ አባል መሆን ስለሚያስገኘው ጥቅም በጥልቀት ማሰብ ያስፈልጋል። የ ‹ብሪክስ› ልምድና የገንዘብ አቅም ከነባሮቹ ተቋማት ጋር ሲወዳደር ዝቅተኛ ሊባል የሚችል ነው። ይህም በማበደር አቅሙ ላይ ተፅዕኖ ሊፈጥር ይችላል።

የልማት አጋሮች የሆኑት ነባሮቹ ተቋማት (የዓለም ባንክ፣ የዓለም የገንዘብ ድርጅት…) ለኢትዮጵያ የ‹ብሪክስ› አባልነት ምን ዓይነት ምልከታ ሊኖራቸው እንደሚችል ጥልቅ ግንዛቤ ሊኖር ይገባል። የእነዚህ ተቋማት ምላሽና ምልከታ አሉታዊ ከሆነ፣ በሀገሪቱ ላይ ከፍተኛ ጫና ሊፈጠር ይችላል። ስለሆነም የብሪክስ አባል መሆን ስለሚያስገኘው ጥቅምና ሊያስከትለው ስለሚችለው ጉዳት በጥልቀትና በጥንቃቄ ማሰብ ያስፈልጋል። ‹አባል መሆናችን ምን ጥቅም ያስገኝልናል? አባል ባለመሆናችንስ ምን ይቀርብናል?› ለሚሉት ጥያቄዎች ምክንያታዊ የሆነ ትንታኔ ማዘጋጀትና በጉዳዩ ላይ ጥልቅ ግንዛቤ መያዝ ይገባል። ጥቅሙን ብቻ በማየትና ከጀርባ ሊከሰቱ የሚችሉ ጉዳቶችን ባለማጤን ለአባልነቱ አዎንታዊ ግምት ብቻ መስጠት አዋጭ አይሆንም›› በማለት ስለ ‹ብሪክስ› አባልነት ጥቅሞችና ጉዳቶች ሚዛናዊ ዕይታና ግንዛቤ መያዝ እንደሚያስፈልግ ያስረዳሉ።

‹ብሪክስ› ኢኮኖሚያዊ ፍላጎትን ከጂኦ-ፖለቲካዊና የደህንነት ፍላጎት ጋር አጣምሮ የተደራጀ እንደሆነ የሚናገሩት ረዳት ፕሮፌሰር ሀብታሙ፣ ጥምረቱ በዓለም ባንክና በሌሎች የፋይናንስ ተቋማትና ሥርዓቶች በኩል በምዕራቡ ዓለም የተያዘውን የፋይናንስ ቁጥጥር የበላይነት ለመገዳደርና ለማስቀረት ጥረት የሚያደርግ በመሆኑ አባልነቱ ሊያስከትለው የሚችለው ጫና ችላ ሊባል እንደማይገባም ይመክራሉ።

‹‹አባልነቱ ሀገሪቱን ለሌላ ጫና እንደሚዳርጋት የሚገልፁ አንዳንድ ተቃውሞዎች አሉ። ጥምረቱ የበለጠ ትኩረት የሚሰጠው ለምጣኔ ሀብታዊ ዓላማ ነው። ‹ጫና ይኖራል› ብሎ እጅን አጣጥፎ መቀመጥም አይቻልም።› ሲሉም ያስገነዝባሉ። ‹‹የጥምረቱ አባል ለመሆን ጥረት እንደተደረገው ሁሉ፣ ከአባልነቱ በሚገባ ለመጠቀምም ስትራቴጂካዊ የሆነ አሠራር መከተልና መተግባር ይገባል። አገሪቱ ከ‹ብሪክስ› አባልነቷ በሚገባ ተጠቃሚ እንዳትሆን መሰናክል የሚፈጥሩ አሠራሮችን ማስተካከልና መዘጋጀት ያስፈልጋል›› ይላሉ።

# ጎሜ

# የተስፋ ተቃርኖ

**ምሕረት ሞገስ**

የጠቆረው ሰማይ የተድቦለቦለ የውሃ እንክብል ወደ ምድር እየወረወረ አዲስ አበባን እያጠባት ነው። የዝናቡን ውሃ የጠገበው መንገድም በንፋስ ሃይል ታጥቦ እንደተሰጣ ልብስ ጠፈፍ ማለት ተስኖት በየቦታው ውሃ አቁሯል። ዘውዴ መታፈሪያ ወደ ማምሻ ግሮሰሪ ሲያቀና፤ እግሩ መርገጫ አጥቶ አንዳንዴ እየዘለለ፤ ምቹ መንገድ ሲያገኝ ደግሞ እየተራመደ ነበር።

ገብረየስ ገብረማርያምም በሌላ አቅጣጫ እንዳይወድቅ እና በየመንገዱ የተጠራቀመውን ውሃ የጠገበ አሽከርካሪ በጎማው ረጭቶ እንዳያበሰብሰው በመስጋት ተጠንቅቆ እየተራመደ ማምሻ ግሮሰሪ ደረሰ። ተሰማ መንግሥቴ ግን ለጊዜው ዕድል ከእርሱ ጋር በመሆኗ፤ ዝናብ አልነካውም። በመንግሥት መኪና ተንጠላጥሎ እና ከጭቃው ተከልሎ፤ የመንገዱ መጨቅየት ሳያንገላታው፣ ሳይጎረብጠው እና ሳያሳስበው ማምሻ ግሮሰሪ ደረሰ። ሶስቱም እንደለመዱት በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ሰፍረው የሚጠጡትን አዘው ጨዋታ ጀመሩ።

ገብረየስ፤ ‹‹ሁልጊዜም አዲስ ዓመት በመጣ ቁጥር ተስፋ ይታየኛል፤ በተስፋ 50 ዓመታቶች አለፉ፤ እየመሸብኝ ቢሆንም ዛሬም እንደሕፃን መስከረም ሲመጣ በብዙ ነገር ላይ ተስፋ አደርጋለሁ። አብዝቼ እደሰታለሁ። በተለይ ስለሀገር እያሰብኩ የሚመጣውን ብሩህ ጊዜ ለማየት እመኛለሁ።›› አለ።

ዘውዴ ደግሞ በተቃራኒው፤ ‹‹አንተ ዕድለኛ ነህ። እኔ ግን አዲስ ዓመት ሲመጣ የተደሰትኩት በልጅነቴ ነው። ነፍስ አውቄ ከብት ማገድ ካቆምኩ በኋላ ደስታ ርቆኛል። ቢነጋም ቢመሽም፤ ወርም ሆነ ዓመት ቢቀየር ተስፋ የማደርግበት አጋጣሚ የለም። ሁልጊዜ የሚታየኝ ጨለማ ነው።›› ሲል፤ ገብረየስ ብቻ ሳይሆን ተሰማም በዘውዴ ንግግር በመገረም ግንባራቸውን ቋጠሩ።

ተሰማ፤ ‹‹እንዴት ለዘመናት ተስፋ ታጣለህ? ሰው ደግሞ ምንጊዜም ቢሆን የሚያገኘውም ሆነ የሚኖረው ባሰበው፣ በተመኘው እና በሠራው ልክ ነው። ባታገኝ እንኳ ተመኝተህ በተስፋ እንደመደሰት እንዴት በጨለማ ሕይወትህን ትገፋለህ?›› ሲል ጥያቄ አቀረበ።

ዘውዴ፤ ‹‹ምን ላድርግ የማየው ሰዎች ሲንገላቱ እና አንዳንዴም ሲታመሙ፤ መዳን እየቻሉ ሲሞቱ። አንዳንዶች ደግሞ እንደውም ሳይታመሙ በሰዎች ጥፋት ሕይወታቸው ሲያልፍ፤ አንዱ በሌላው ላይ የጭካኔ አሰቃቂ ተግባርን ሲፈፅም ብቻ ነው። ተስፋ ማድረግ ቀርቶ፤ ለፈጣሪዬ የምፀልየው አደራ ባልተገባ መልኩ በሰው እጅ ላይ ጥለህ እንዳታሰቃየኝ እያልኩ ነው።›› በማለት ምላሽ ሰጠ።

ገብረየስ በበኩሉ ዘውዴን እየተመለከተ፤ ‹‹ዋነኛው ችግርህ ይሔ ነው። ሁልጊዜም ማማረር ይቀናሃል። ታክሞ ከዳነው ይልቅ፤ የሚታይህ ታሞ የሞተው ብቻ ነው። ከተሠራው በጎ ነገር ይልቅ የጠፋውን ነገር ማየት ትወዳለህ። ነገር ግን በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ እያማረሩ በሩቅ አይቶ ከማለፍ ይልቅ ገብቶ ችግር ለማቃለል መሞከር ይሻላል።

አንዳንዱ ሁሉንም ነገር በቸልተኝነት እያየ በራሱ ጉዳይ ላይ ሳይቀር ታዛቢ ለመሆን እየሞከረ፤ ለቤተሰቡ፣ ለዘመዶቹ እና ለሀገሩ ባይተዋር እየሆነ እንደውጪ ሰው አስተያየት ይሰጣል። አስተያየቱ ደግሞ ምሬት አዘል ነው። በዚህም የራሱን ብቻ ሳይሆን የብዙዎችም ተስፋ ያጨልማል።›› አለ።

ዘውዴ ቀዝቀዝ ብሎ ተስፋ በቆረጠ ድምፅ፤ ‹‹ሰው ላይ መፍረድ ቀላል ነው። እኔ በሕፃንነቴ ያየሁት አንዱ የሌላውን ደም እበቀላለሁ ብሎ ሲገድል፤ መገዳደል ጀግንነት ሆኖ ሲነገር ነው። አጎቶቼ ያለ በቂ ምክንያት ሰውን ገድለው ልጆቻቸውን ሜዳ ላይ በትነው በረሃ ሲገቡ ጀግና ተብለዋል። ይህንን እያየሁ አድጌ ምን ተስፋ ላድርግ?›› ሲል የእርሱ በሁሉም ነገር ላይ ተስፋ መቁረጥ ትክክል መሆኑን ለማስረዳት ሞከረ።

ተሰማም ለዘውዴ ‹‹ችግሩ በአስተዳደግህ የመጣብህን ተፅዕኖ ተቋቁመህ ራስህን ለመቀየር አለመሞከርህ ነው። ይህን ተከትሎ ተጨባጭነት የሌለው ስጋት ውስጥ ገብተህ ዘመንህን እያሳለፍክ ነው። ቀድሞም ቢሆን

> **አንዱ ጥግ ይዞ ተጠቅቻለሁ ሲል፤ ሌላኛው ሌላኛውን ጥግ ይዞ እርሱም ተጠቅቻለሁ ይላል። ማን እንዳጠቃ አይታወቅም። አንዱ ጥግ ይዞ የእኔ ሃሳብ ብቻ ይሰማ፤ እኔ ብቻ ትክክል ነኝ ሲል፤ በሌላ ጫፍ ያለውም በተመሳሳይ መልኩ እኔ ብቻ ልሰማ ይላል**

ጥላህንም አታምነውም፤ መጠራጠር መለያህ ነው። ማጥላላትን የምታየው እንደትልቅነት ነው። ይሔ በአንተ ላይ በቅርብ በግልፅ ስላየን ስለአንተ ገለፅን እንጂ፤ ይሔ ችግር በሀገር ደረጃ በብዙ ሰዎች ላይ የሚታይ እና ሀገር ላይም ከባድ ቀውስ እያስከተለ ያለ ጉዳይ ነው። እዚህ ላይ መሠረታዊ ለውጥ ያስፈልገናል።›› አለ።

ገብረየስም፤ ‹‹እኔም እንደማምነው ሰበብ እየፈለጉ ማጥላላት፤ በሌላ በኩል ሰበብ እየፈለጉ የራስ ወገን እንደተጠቃ እየጠቀሱ ማስተጋባት አያዋጣም። እያዳሉ መጥቀምም ሆነ መጉዳት ትርፍ የለውም። እኛ በዓለም ደረጃ መገለጫችን ኢትዮጵያዊነታችን ነው። ስለምን በሀገር ውስጥ በመንደር ደረጃ ስላለው መገለጫችን በመጨነቅ ጊዜያችን ባልተገባ መልኩ እንደምናሳልፈው ግልጽ አይደለም። የሚያዋጣው ከመማረር ይልቅ ተቀላቅሎ መስራት ነው። የሰው ሞት ወይም የሰዎች እኩል ያለመታየት ጉዳይ የሚያበሳጨን ከሆነ፤ ጥረት አድርገን ችግሩን መፍታት እንጂ ተነጥሎ ጨለማ ውስጥ መንከባለል ትርፍ የለውም።›› አለ።

ዘውዴ ‹‹እኔ ሰው ሰው በመሆኑ ብቻ ክብሩ እና ነፃነቱ ሊከበርለት ይገባል የሚል እምነት አለኝ። ይህንን ማለት ደግሞ ወንጀል አይደለም። አንድ ሰው መብቱ ይከበርለት ሲል ከጎሳ ወይም ከብሄር ጋር መወሰድ የለበትም። ስለአንድነት በማሰብ አንድ እንሁን ማለቱን ተከትሎ ጎራ እየለዩ መዋቀስም አይገባም። እያንዳንዱን ሃሳብ ለመግለፅ ሲሞከር እንኳ በራሳቸው ውስጥ ጎጠኝነት አብቦ ቤቱን የሠራባቸው ሰዎች፤ ሁሉንም ሰው እና ሁሉንም ሃሳብ ከጎጥ አንፃር ያቀርቡታል። በእርግጥ ይህንን አስተውዬ በጣም ተከፍቻለሁ። ተስፋ እስከማጣት ደርሻለሁ። በዚህ ምክንያት ምንም ላለመናገር አፌን ዘግቻለሁ።›› አለ።

ገብረየስ ቀበል አድርጎ፤ ‹‹አንተ ብቻ አይደለህም፤ ከአንተ ጋር በተመሳሳይ መልኩ ብዙ ተስፋ የቆረጡ ይኖራሉ። ነገር ግን ችግሩም እኛ እንደምንገልፀው ይህ ብቻ አይደለም። አንዱ ጥግ ይዞ ተጠቅቻለሁ ሲል፤ ሌላኛው ሌላኛውን ጥግ ይዞ እርሱም ተጠቅቻለሁ ይላል። ማን እንዳጠቃ አይታወቅም። አንዱ ጥግ ይዞ የእኔ ሃሳብ ብቻ ይሰማ፤ እኔ ብቻ ትክክል ነኝ ሲል፤ በሌላ ጫፍ ያለውም በተመሳሳይ መልኩ እኔ ብቻ ልሰማ ይላል።

ጎራ ፈጥሮ በቡድን መደበላለቅ ለማንም አይጠቅምም። ጎሳ ውስጥ ከመነከር ወጥቶ እና ልዩነትን እያጠበቡ አንድነትን እያጎሉ በጋራ ለማደግ ማሰብ ይበጃል። እዚህ ላይ መሥራት እንዳለበት አይካድም። ይህ እንዲሆን ደግሞ እኔ እና አንተን ጨምሮ እያንዳንዱ ግለሰብ ከራሱ መነሳት አለበት።›› ሲል ሃሳቡን ገለፀ።

ተሰማም የእነርሱን ሃሳብ የሚያጠናክር በሚመስል መልኩ፤ ‹‹ትክክል ናችሁ። ብዙዎች ውስጣቸው ከእናንተ ሃሳብ ጋር የተስማማ ነው። ነገር ግን ሁሉም በልክ መሆን አለበት። እንደዘውዴ ለዘመናት ተስፋ መቁረጥ አይገባም። ሰዎች ሃሳባቸውን ሲያቀርቡም ሆነ እምነታቸውን ሲያራምዱ ተቀባይነት ሊኖርም ላይኖርም ይችላል። ተቀባይነቱን ለማግኘት ተጨባጭ ማስረጃን ይዞ መቅረብ እና አቀራረቡን የተሻለ ማድረግ ይገባል። ጊዜ እየመረጡ በጊዜ ላይ መሸጎጥ እና ሃሳብን ጊዜ እየመረጡ በማቅረብ ያልተገባ ትርፍ መሰብሰብ ብዙ ርቀት አያስጉዝም።›› አለ።

የገብረየስ ሃሳብ ግን ‹‹በዋናነት በኢትዮጵያ ለዘመናት እየታየ ያለው እና የብዙዎችን ተስፋ ያጨለመው በተናጥል ሸኩቻ ውስጥ ተወትፈው የሚሽከረከሩ በመብዛታቸው ነው። የጋራ ግብ በማስቀመጥ በጋራ ከማደግ ይልቅ፤ አንዱ ሌላውን እየጎተተ ሲቀብር ዘመናቶች ተቆጥረዋል። ይህችን ሀገር የመሩ እና በዚህች ምድር ላይ የኖሩ ሰዎች ቢሰሩም ከሰሩት ይልቅ ያልሰሩትን በማውራት ብዙ ጊዜያቶች አልፈዋል።

የትናንቱን ብቻ እያውጠነጠኑ ማዳመጥ ዛሬን እንደሚያስረሳ ያልተገነዘቡ ሰዎች ተስፋ ማድረግ ተስኗቸዋል። በእርግጥ የትናንቱ መረሳት ባይኖርበትም በልኩ መነሳት አለበት። መቀየር በማይቻለው ትናንት ላይ ተጣብቆ ከልክ በላይ ማላዘን ሁሉንም ያከስራል። የዛሬን እየሠሩ ለነገ ተስፋ ማድረግ ጤነኝነትን ያመለክታል። እንደኔ እምነት ፍፁም ተስፋ ማጣት ግን እጅግ ከባድ ነገር ነው›› አለ።

ዘውዴ በበኩሉ፤ ‹‹አዳማጭ መሆን እንችላለን ብላችሁ ካመናችሁ እና እኔን ለማዳመጥ ከፈለጋችሁ በደንብ ብታዳምጡኝ ይሻላል። ሰው ወደደም ጠላ የሆነ ሰው ቤተሰብ ነው። ምርጫ የለውም፤ ያ ቤተሰብ ድሃም ሆነ ሀብታም፤ ባለጌም ሆነ ጨዋ፤ የተዋረደም ሆነ የተከበረ ብቻ ለግለሰቡ ቤተሰቡ የጋራ መገለጫው ነው። በዚህ መገለጫው ላይ አያገባኝም ማለት የራስን ክብር መጠበቅ አለመቻል ነው። ለራስ ክብር ማጣት ደግሞ የህልውና ጉዳይ ነው። ክብር ማጣት ህልውናን ከማጣት ተለይቶ አይታይም። ቢያንስ ሰው ተቀናጥቶ ደስታ ውስጥ መዋኘት ቢያቅተውም ተከብሮ ፤በልቶ ፤ጠጥቶ እና ለብሶ መኖር የሚችልበት ሁኔታ ሊፈጠር ባይችል እንኳ ስለደህንነቱ ማሰብ፣ መጨነቅ እና መጠየቅ ይጠበቅበታል። በዚህ በኩል ማሰብህ፣ መጨነቅህ እና መጠየቅህ ትክክል አይደለም ካላችሁ ለእኔ እናንተ ትክክል አይደላችሁም።›› ሲል አቋሙን ገለፀ።

ገብረየስ በበኩሉ፤ ‹‹በእርግጥ አንተ እንደጠቀስከው ምንም ጥያቄ አታንሳ አላልንም። መጠየቅ ትክክል ነው። ነገር ግን በዚህ ደረጃ ተስፋ መቁረጥ አይገባም። የራስን ክፍተትም በባህል እና በመንግሥት ላይ እያላከኩ መሸፋፈን ጠብ የሚያደርገው ነገር የለም። ምክንያቱም ዓለም የምትሰጠን በሠራነው፤ በለፋነው፤ በከፋነው እና ደግ በሆነው ልክ ነው ይባላል። አውሮፓ እንደምን ሰለጠነች ከተባለ መነሻቸው እና መድረሻቸው ሥራ በመሆኑ ነው። ስለሠሩ ለእነርሱ ዓለም ከፍላቸዋለች፤ በተቃራኒው እኛ ደግሞ በእነርሱ መጠን ስላልሠራን ወይም ዛሬ ላይ ከመሥራት ይልቅ በማይሆን መንገድ ተጉዘን ባለፈው ታሪክ ላይ ቆመን ስለቀረን ወይም ቆመን ባንቀርም ጉዟችን እጅግ አዝጋሚ በመሆኑ ወደ ኋላ ቀርተናል። ስለዚህ አሁን መፍትሔው ላይ በደንብ መሥራት ነው።›› አለ።

ተሰማ በበኩሉ መፍትሔ የሚለውን ሰነዘረ። ‹‹በተቻለ አቅም ለመሥራት፤ ሥራ ሲበላሽም ለመወያየት እና ለመከራከር መሞከር ይሻላል። መመካከር እና መወያየት ክፋት የለውም። በውይይት ብዙ ጥሩ አዳዲስ ሃሳቦች ይገኛሉ። ነገር ግን መከራከርም ሆነ መወያየት ሚዛናቸውን ጠብቀው መከወን አለባቸው። ዋነኛው ጉዳይ በመመካከር በጋራ ዓላማ ፤ ለጋራ ሀገራችን መሥራት ነው። መንግሥትንም ሆነ ማንንም ከማማረር በፊት ሌላውን ለመረዳት እና እዛ ጫማ ውስጥ ሆኖ ለማሰብ መሞከር ያስፈልጋል።

ሃላፊነትን የማይወስዱ የቤተሰባቸው ጉዳይ ላይ ሳይቀር አያገባኝም የሚሉ ዳተኞች በበዙበት ሀገር ውስጥ፤ ሕዝብ ማስተዳደር እና መምራት ከባድ ነው። ብዙዎች ለሙያቸው ተገዢ ሳይሆኑ፤ በተጣለባቸው ሃላፊነት ሕዝብን ማገልገል ሲገባቸው ባልተገባ ቦታ ላይ ተገኝተው ጊዜያቸውን እና ገንዘባቸውን በማማረር ላይ ካሳለፉ ጥፋቱ የማን ነው? ብሎ ሁሉም ራሱን መጠየቅ አለበት። ተስፋ ቆርጦ አሰልቺ ሕይወትን ከመግፋት ይልቅ፤ ሁሉም በየደረጃው ሃላፊነቱን ቢወጣ ብዙ የሚያማርር አይኖርም ነበር።

የመሥሪያ ዕድሉን አግኝተው የሚጠበቅባቸውን ከመሥራት ይልቅ ታዛቢ ሆነው የገዛ ሥራቸውን የሚያጥላሉ ሰዎች ስለመኖራቸው አይካድም። ከሁሉም ነገር ቀድሞ ደህንነት ሊሰማን ይገባል። ማህበራዊ ደህንነት ያስፈልጋል፤ ደህንነት ሳይኖር ስለምግብ፣ ስለትምህርት፣ ስለጤና እና ስለንፁህ መጠጥ ውሃ መናገር ቅንጦት ነው የሚሉ አሉ። በእርግጥ ደህንነት ሳይኖር ስለሙያ ተገዢነት መስበክ የዋህነት ነው የሚሉም አይጠፉም። ነገር ግን በምንም መልኩ ከስጋት ተስፋ ይሻላል፤ እጅግ የተወሳሰበ ችግር መኖሩን በማሰብ አንዱ የሌላውን ሥራ መደገፍ ይኖርበታል።

ሀገር የምታድገው በምሬት እና ተስፋ ቆርጦ በመሸሽ፤ ሃላፊነትን ባለመውሰድ ሳይሆን በሥራ እና በትጋት ነው። የተሠራው ሥራ ትልቅ ውጤት ያስገኛል ብሎ ተስፋ በማድረግ ነው። ሁሉም ከሥራ ይልቅ ወደ ምሬት ራሱን ከመራ ጉዞ ወደ ፊት ሳይሆን ወደ ኋላ ነው። በአዲስ ዓመት ተስፋ እናድርግ፤ እንስራ፤ ከዛም ምናልባትም የአገሪቱ ችግር ከነሰንኮፉ ተነቅሎ ይወጣል።›› ሲል አዲስ ዓመት ተስፋ የሚደረግበት እና ትልቅ ውጤት የሚገኝበት እንጂ፤ ምሬት የሚሰማበት እና ተስፋ የሚቆረጥበት መሆን እንደሌለበት አመልክቶ ሃሳቡን ቋጨ።

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

## መስከረም እና ኪነ ጥበብ

**ዋስልኝ አየለ**

የመስከረም ወር ለየት ይላል። የሬዲዮና ቴሌቪዥን ማስታወቂያዎችን ልብ ብላችሁ ከሆነ የበዓል ይዘት የሚኖራቸው ለእንቁጣጣሽ ወይም መስቀል በዋዜማው ወይም በማግስቱ ብቻ አይደለም። መስከረም ወሩን ሙሉ ደማቅ ነው። የማስታወቂያዎችም ሆነ የፕሮግራሞች ማጀቢያዎች በመስከረም ወር ላይ የሚያተኩሩ የሕዝብ ወይም የታዋቂ ከያኒያን የጥበብ ሥራዎች ናቸው።

መስከረም የተፈጥሮ ጥበብ የሚታይበት ልዩ ወር ነው፤ ይህ የተፈጥሮ ጥበብ ደግሞ ሰዎችም እንዲጠበቡ አደረጋቸው። አዳዲስ ነገሮች የሚታዩበት ስለሆነ አዲስ ፈጠራ ለማሰብ ከያኒያንን ሳያነሳሳ አይቀርም። በተፈጥሮ የክረምት ወራት አልቆ ፀሐይ የሚወጣበት፣ አበቦች በየመስኩ የሚፈኩበት ነው። መስከረም ከክረምቱም ከበጋውም ወቅት የተለየ ነው። በክረምት «እኝኝኝ...» ያለ ዝናብ እና ብርድ ነው። መሬቱም ጭቃ ነው። በበጋ ወቅት ደግሞ የነደደ ፀሐይና ሙቀት ነው። መሬቱም አቧራ ነው። መስከረም ግን ከሁለቱም ነፃ የሆነ ነው። የከፋ ጭቃ የለም፤ የከፋ አቧራ የለም። የከፋ ብርድ የለም፤ የከፋ ሙቀት የለም። በእነዚህ ባህሪያቱ ነው የተፈጥሮ ውበት የሆነው። ከወራት ሁሉ ተለይቶ ለሰው ስም እንኳን ይውላል።

የመስከረም ወርን በዚህ ልክ እንዲደጋገም እና እንዲህ ስመ ጥር ያደረገው ተፈጥሯዊ ባህሪውን ምክንያት በማድረግ የኪነ ጥበብ ሥራዎች ናቸው። መስከረም በራሱ ጥበብ የሆነ ወር ነው። ለዚህም ነው በኪነ ጥበብ ሥራዎች ውስጥ ስሙ ተደጋግሞ የሚጠቀሰው። ምንም እንኳን ዘፋኞች ውስጥ ቢበዛም፣ በገጣሚዎች፣ በተዋናዮች፣ በደራሲዎች... ከወራት ሁሉ በበለጠ የተጠቀሰ ነው። የጥበብ ሰዎች አበባ ሲያዩ ሀሳብ ይመጣላቸዋል ማለት ነው። ወደ ግጥሞችና ዘፈኖች ከመሄዳችን በፊት ግን መስከረምን መቼት ያደረጉ የኪነ ጥበብ መጀመሪያ የሆኑትን የስነ ቃል ውጤቶችን እንመልከት።

በምሳሌያዊ ንግግሮች ውስጥ መስከረም ተደጋግሞ ይጠራል። የወሩን ተፈጥሯዊ ባህሪ ከሚገልጸው ምሳሌያዊ ንግግር እንጀምር። «የመስከረም ዝናብ ከላም ቀንድ ይለያል» ይባላል። የምሳሌያዊ ንግግሩ ትርጉም የመስከረም ዝናብ ሁሉንም ያማከለ አይደለም ለማለት ነው። የላም ቀንድ በጣም የተጠጋጋ ነው። አንዱ ጋ ዝናብ ዘንቦ አንዱ ጋ ላይዘንብ ይችላል ማለት ነው። ምሳሌያዊ ንግግሩ በጣም የተጋነነ ቢሆንም የመስከረም ዝናብ ግን እንዲህ ነው። በጣም የተቀራረቡ ቦታዎች ላይ (ለምሳሌ አራት ኪሎ ዘንቦ ፒያሳ) ላይዘንብ ይችላል። ይህ አባባል ጥቅል ሁኔታውን ለመግለጽ እንጂ ሁሌም እንዲህ ይሆናል ማለት ግን ላይሆን ይችላል፤ ለምሳሌ ሰሞኑን እንደገና ክረምት መስሏል።

«መስከረም በአበባው ሰርግ በጭብጨባው» የሚባል ምሳሌያዊ ንግግርም አለ። ጭብጨባ የሰርግ መለያ እንደሆነ ሁሉ የመስከረም መለያውም አበባ ነው። አንድ መንገደኛ እየሄደ የሆነ መንደር ውስጥ ጭብጨባ ከሰማ «እዚህ ግቢ ሰርግ አለ ማለት ነው» ብሎ ይገምታል። እርግጥ ነው ነገሩ ሰርግ ብቻም ላይሆን ይችላል፤ በሌላ የድግስ ፕሮግራምም ይጨፈራል። ዋናው ግን ለሰርግ ነው። የመስከረም ወርም እንደዚሁ ነው። ስለመስከረም በተለያየ መረጃ የሚያውቅ አንድ የውጭ አገር ሰው ኢትዮጵያ መጣ እንበል። ኢትዮጵያ ሲገባ ጋራ ሸንተረሩ በአበባ ተንቆጥቁጦ ካየ «የመስከረም ወር ነው ማለት ነው» ይላል።

ሌላው ገናና ምሳሌያዊ አነጋገር ደግሞ «ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባም» የሚባለው ነው። መስከረም አዲስ ዓመት ስለሆነ ባለፈው የተከናወኑ አስገራሚ ነገሮች ይታወሳሉ። የዓመቱ የመጨረሻ ወር ላይ ያሉት የመጨረሻ ሳምንታት የመገናኛ ብዙኃን ሽፋን የሚሰናበተውን ዓመት አስገራሚ ክስተቶችን ይዘግባሉ። «ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባም» የሚባለው ለዚህ ነው። በዓመቱ ውስጥ የሆነ አስገራሚ ነገር ስለማይጠፋ ማለት ነው። ይህ በውጭው ዓለምም የተለመደ ነው። «ጉድ ሳይሰማ ጥር አይገባም» የሚል አባባል ይኑራቸው አይኑራቸው ባላውቅም በታህሳስ ወር መጨረሻ ላይ የተሰናባቹን ዓመት ክስተቶች ያስታውሳሉ።

የሕዝብ የስነ ቃል ጥበብ ከሆኑት «ለምኝ ሰኔ በጋው መስከረም ክረምቱ» የሚባል ምሳሌያዊ ንግግርም አንዱ ነው። በእንዲህ አይነት ጥበባዊ ለዛ መልዕክት ያስተላልፋሉ ማለት ነው። አሁንም ሰኔ እና መስከረምን ልናነፃፅር ነው። «ለምኝ ሰኔ በጋው መስከረም ክረምቱ» የተባለው የሰኔ ወር የክረምት መግቢያ ሲሆን መስከረም ደግሞ የክረምት መውጫ ነው። ምኝ ወይም ሰነፍ የሆነ ሰው በሰኔ ገበሬው ሁሉ ሲሯሯጥ እሱ ዝም ይላል። መስከረም ላይ ተፍ ተፍ ቢል ከየት ይመጣል! «ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ» እንደሚባለው ማለት ነው።

ሌሎች ምሳሌያዊ ንግግሮች ደግሞ በቃል ግጥም የሚባሉ ናቸው። የቃል ግጥም ሆነው እንደ ምሳሌያዊ አነጋገር የሚያገለግሉ አሉ። ያ ማለት ለዘፈንና እንጉርጉሮ ሳይሆን በጨዋታ (በወሬ) መካከል ሀሳቡን ለማዳበርና ግልጽ ለማድረግ ይጠቀሙታል ማለት ነው።



**መስከረም ሲጠባ**
**አደይ ሲፈነዳ**
**እንኳን ሰው ዘመዱን**
**ይጠይቃል ባዳ**

ይሄን የቃል ግጥም በብዙ የባህል እና የበዓል ዘፈኖች ውስጥ ስለምንሰማው የዘፈን ግጥም ይመስለን ይሆናል። ዳሩ ግን የንግግር ምሳሌያዊ አነጋገር ነው። በወግ መካከል የሚያወሩት ነው። ምናልባትም ዜማ ላይኖረውም ይችላል፤ መድረክ ላይ በሚነበብ ግጥም አይነት በወሬ መሃል ያስገቡታል። የመስከረምን ጸዳልነት ለመግለጽ ነው። በተለይም ገበሬዎች በክረምት ከፍተኛ የሥራ ውጥረት ውስጥ ስለሚሆኑ ዘመድ ከዘመድ እንኳን አይገናኙም። በሌላ በኩል ደግሞ አብዛኛው የገጠሪቱ የአገሪቱ ክፍል (በተለይም ቀደም ባሉት ዘመናት) ድልድይና የመኪና መንገድ ስለሌለ የሚገናኙት የወንዝ ውሃ ሲጎድል ነው። ወንዞች ከመስከረም በኋላ ስለሚጎድሉ ዘመድ ከዘመድ ይገናኛል። እንኳን ዘመድ ባዕዳም ይጠየቃል ያሉት ለዚህ ነው።

**ያረሰማ ጎበዝ**
**እርፍ የነቀነቀ**
**ወፍጮው እያጓራ**
**መስከረም ዘለቀ**

አዝማሪዎች በሰርግና በሌሎች ዝግጅቶች ላይ ገበሬውን ለማወደስ ይጠቀሙታል። ከአዝማሪዎች በፊት ግን የህዝብ ግጥም ነው። እንደማንኛውም ምሳሌያዊ ንግግር በወግ መካከል ይጠቀሙታል። በነገራችን ላይ ይሄ ምሳሌያዊ ንግግር (የቃል ግጥም ልንለውም እንችላለን) ከመስከረም ወር ይልቅ በሰኔና በሐምሌ ይደጋገማል። ምክንያቱም ሰነፍና ታታሪ ገበሬን ለማነጻጸር የሚያገለግል ነው። ሰነፍ ገበሬ በሰኔ እርሻ ላይ ተፍ ተፍ አይልም፤ ጎበዝ ገበሬ ደግሞ ተፍ ተፍ ይላል። ሰነፉ ገበሬ ጠንክሮ ባለመሥራቱ በሐምሌና ነሐሴ ይቸገራል (የሚበላው ያጣል)። ጎበዝ ገበሬ ግን በክረምት ጠንክሮ ያረሰው ዓመቱን ሙሉ ስለማያልቅ ከመስከረም መስከረም ወፍጮው እያጓራ ይዘልቃል ማለት ነው።

ከቃል ግጥሞችና ምሳሌያዊ ንግግሮች ስንወጣ ደግሞ ደራሲዎችን፣ ገጣሚዎችንና ዘፋኞችን እናገኛለን። ስለመስከረም ብዙ ተዘፍኗል። ምናልባት ግን በዘፈኖች ውስጥ የግጥሞች መደጋገም ይኖር ይሆናል፤ በብዙ የባህል ዘፈኖች ውስጥ የህዝብ ቃል ግጥም ስለሚበዛ መደጋገሙ ያጋጥማል። በሁሉም ውስጥ አበባ ይኖራል፣ ጋራ ሸንተረሩ በአደይ አበባ መድመቁ ይገለጻል።

ወደ ገጣሚዎች ስንሄድ በተደጋጋሚ የሚጠቀሰው እንግዲህ የመንግስቱ ለማ ነው። የመስከረም ወርን ባህሪ የሚገልጽ ነው።

**የመስቀል ወፍና**
**የአደይ አበባ**
**ቀጠሮ እንዳላቸው**
**መስከረም ሲጠባ**
**ማን ያውቃል?**

የመስቀል ወፍ እና የአደይ አበባ አንዳች አስማት ያላቸው ነው የሚመስለው። የሚታዩት በመስከረም ወር ብቻ ነው። የመስቀል ወፍ ላይ ግን አንድ ሳይንሳዊ መላ ምት አለ። ወፏ ከየትም የመጣች ወይም አዲስ የተፈጠረች ሳትሆን የነበረች ናት ይባላል። የክረምት ወር አልፎ መስከረም ሲጠባ በሚወጣው ፀሐይ ቀለሟ ይቀየራል የሚል መላ ምት ይጠቀሳል።

የአደይ አበባ ነገር ግን አሁንም ምሥጢሩ አልተገለጸም። መለኮታዊ ምሥጢር ያለው ይመስላል። ቃልኪዳኑን ጠብቆ መስከረም ላይ ነው የሚያብብ። ሌሎች የሳር እና የተክል አይነቶች ዝናብ ወይም የመስኖ ውሃ ካገኙ ይበቅላሉ። በበጋ ወቅት በመስኖ ዳርቻ ይታያሉ። አደይ አበባ ግን ዓመቱን ሙሉ ዝናብ ቢሆን በበጋ ወቅት አይበቅልም፤ በየትኛውም የመስኖ ዳርቻ አደይ አበባ አይታይም፤ ይህ ራሱ ተፈጥሯዊ ጥበብ ነው።

በመስከረም ላይ የተሰሩ በርካታ የኪነ ጥበብ ሥራዎች ናቸው ያሉት። ዘፈኖችንም ግጥሞችንም እንዘርዝር ቢባል ሙሉ ጋዜጣው አይበቃም። «ደስ ይላል መስከረም» በሚለው ደስ የሚል የባለቅኔ ሙሉጌታ ተስፋዬ ግጥም እንሰነባበት። ደስ የሚል መስከረም ይሁንላችሁ!

**ደስ ይላል መስከረም**
**በግርሻ ጣይ ሰርዶ ነቅሉ በሚያዚያ ንሽ ተርበጥብጦ**
**በግንቦት ሐሩር ተቀቅሉ በፀሐይ አብስሉ በዝናብ አብቅሉ**
**ከወዳጅ ከዘመድ ተቀላቅሉ**
**ባዝራን ከአህያ አዳቅሉ**
**በባለ በርሸት ሽልም በቅሉ**
**ተፈናጦ አብሮ ገስግሶ**
**ጅራፍ ግርፊያ ሆያ ሆዬ ቡሄ በሉ ተጫውቶ**
**ኪዳነ ምሕረትን አንግሶ ደግሞ በወሩ ለአስተሮዮው**
**ግሼን ማሪያም እማአርያም ደጀሰላም ደርሶ**
**ለመሳለም**
**‹‹እዮሃ አበባዬ መስከረም ጠባዬ**
**ዐደይ ስምስም ስኔ እንዳንቺ የለም...››**
**እያሉ ንጥቂያ**
**ከጀንበር መፍለቂያ እሥከ ጀንበር መጥለቂያ**
**አለሳ ነቅሉ ባሕር እንጉዳይ**
**ጀግና ሰው ገዳይ**
**አካል እንጉዳይ**
**እያሉ ሲያንጎራጉሩ!**
**ደስ ይላል መስከረም!**
**ቡቃያው ጣል ከንበል ሲል**
**ሹሩባዋ ወርዶ እንዲያ ሲዘናፈል**
**ልቤ እንደበቆሉ ያድራል ሲ ፈ ለ ፈ ል**
**በቀጭን ተሰርታ ሥትል ዘንከት ዘንከት**
**ጃሉ ሲል ሲያነጋ አገር በመለከት**
**ለመስቀል ጠንሰሶ በማድጋ ገንቦ ለእንግዳ ቀንሶ**
**በሞቴ አፈር ስሆን እያለ ሲያጋፍር**
**ጥርስ እንጎቻ አስፍቶ አሞጭ በመሰለው እርጎ ፍርፍር**
**እንኳን ሳቅ ጨዋታው ድብድቡ ልፊያው**
**ድገሙኝ ያሰኛል ሰፈፍ የለሽ ሞገድ መደዶ ዘር ዜማ**
**ሲቆረቆር ክትፊያው**
**ደስ ይላል መስከረም!**
**የሽንብራ እሸት እየጠረጠሩ**
**የልጅነት ሚዜ ‹‹ሽረ አደዋ ክንዴ›› እያሉ እየጠሩ**
**አብሮ ወፍ ጥበቃ ማማ ላይ ተሰቅሉ**
**ካፊያውን በገሳ በአንድ ተጠልሉ**
**እሳት አቀጣጥሉ በቆሉ ጠባብሶ**
**አየሁ አላየሁም... ሰማሁ አልሰማሁም**
**በላልቶ አፍ አብሶ**
**ለስልሶ አስፈትሉ የእናት ኩታ ለብሶ**
**ላዋቂ ተልኮ ለልጅ ተጎናብሶ**
**ደስ ይላል መስከረም!**
**እንደቢራ ቢሮ አበባ ለአበባ ዐደይ እንቡር እንቡር**
**በፍቅር ለመክረም**
**ደስ ይላል መስከረም!**
**ወፉ ከነ ጎጆው እሥከ መናጆው**
**ንቡ ከነ ቀፎው መረባ ከነ እርፎው**
**በዐደይ ስምስም ክብር ለመስከረም ክብር**
**ቅዱስ! ቅዱስ! ቅዱስ!**
**የዓመት አሥራት ሲያፈስ**
**ሲያስገባለት ግብር**
**በዝማሬ ሲያብር**
**አንጀት ሲበረብር**
**ደስ ይላል መስከረም!**
**ተዋዶ ወዶ ተወሕዶ ያንጀት ተፈቃቅዶ**
**ባንድ አብሮ ለመክረም**
**ደስ ይላል መስከረም!**
**ለቅኔ ዘረፋው ጠፈፍ ሲል ፈፋው**
**የቆሉ ተማሪ ያ ተመራማሪ**
**የወላዲት አምላክ የድንግል አዝማሪ**
**ያ ደበሉ ለባሽ!**
**በእግዚትነ ማሪያም! እባካችሁ እባሽ እባካችሁ ቁራሽ**
**እ ያ ለ ሲለምን**
**ከጥንቅሹ ቅንጥሽ ማሩቴ ባይሰጠው**
**አይቀር መደንገጡ አራሽ አባ ወራሽ ማብላት ያሰለጠው**
**የማይለወጠው**
**በዐይኑ እየመዘነ በልቡ እማይመርጠው**
**ገሩ ባላገሩ**
**ያ ባለሞፈሩ ያ ባለዘገሩ**
**በሞቴ ነው ቋንቋው ስሞት ነው ነገሩ**
**ደስ ይላል መስከረም!**
**ወዶ ተወሕዶ ያንጀት ተፈቃቅዶ**
**አንድ ልብ አቅዶ**
**አንድ ላይ ለመክረም**
**ደስ ይላል መስከረም!**
**ጥቅምትና ኅዳር ቢያዋውል ምንጭ ዳር**
**ታኅሳስና ጥር ዐውድማ አስለቅልቆ ጥሪት እሚያስቋጥር**
**የካቲት መጋቢት መኸር አስከትቶ ቢያበስል እንደ ዐቃቢት**
**ሚያዚያና ግንቦቱ ተርቲበኛው ቀርቦ ወርዶ ረከቦቱ**
**የላም ልጅ በዋንጫ ቢቀርብ ሥልባቦቱ**
**ሰኔ ሐምሌ ነሐሴ እንደ ቄስ ምናሴ**
**እያረበረበ ደግሞ እየወረበ**
**ሰማይ በበረቀ ታርሶ ርሶ ሲስረቀረቅ**
**ከራሱ እስኪታረቅ**
**ሁሉም እንደ ግብሩ**
**ሁሉም እንደ ሙያው!**
**አሥራ ሁለቱም ወር**
**እዮሃ አበባዬ መስከረም ሲጠባ**
**ያኔ ነው ገቢያ**
**ያኔ ነው መታያው**
**ያኔ ነው ማባያው**
**ደስ ይላል መስከረም!**

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## ስባለውለታዎች የተበረከተው የአረጋውያን ማዕከል

**እየሩስ ተስፋዬ**

በጉብዝና ወራቸው እውቀትና ጉልበታቸውን ሳይሰስቱ ባላቸው ጊዜ ሁሉ ኃላፊነታቸውን በሚገባ ተወጥተዋል፣ ሀገራቸውን በሚገባ አገልግለዋል። የዛሬዎቹ አረጋውያን ትውልድን ቀርጸው፤ ሀገርን አቅንተዋል። ሀገር ለመውረር የመጣን ጠላት በብርቱ ክንዳቸው አሳፍረው መልሰዋል። ድልድይ ሆነው ይህችን ሀገር ለዛሬ አድርሰዋል። የከፈሉት መስዋዕትነት ጥቂት አይደለም። እነዚህ የሀገር ባለውለታዎች በእድሜያቸው አመሻሽ ወድቀው እንዳይቀሩ በግለሰብም ይሁን በመንግሥት ደረጃ የተለያዩ ጥረቶች ሲደረጉ ይስተዋላል።

ባለፈው መስከረም 03 ቀን 2016 ዓ.ም ግንባታው ተጠናቆ ለምርቃት የበቃው ‹‹የአረጋውያን መጦሪያ መጠለያና እንክብካቤ ማዕከል›› ለዚህ አንዱ ማሳያ ነው። የሰንሻይን ኢንቨስትመንት ግሩፕ አካል የሆነው ‹የሰንሻይን ፊላንትሮፊ ፋውንዴሽን› ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተሰጠው 30ሺ ካሬ ሜትር ላይ በ634 ሚሊየን ብር ወጪ ማዕከሉን ገንብቷል። የተገነባው ማዕከልም ለሰባት መቶ ሰላሳ አረጋውያን እንክብካቤ የማድረግ አቅም አለው።

የከተማዋ ባለሀብቶች ማህበራዊ ኃላፊነት መወጣትን ባህል እያደረጉ እንደሚገኙ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በአዲስ አበባ ለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ሰሚት አካባቢ የተገነባውን ማዕከል ምሳሌ አድርገው ተናግረዋል። ሰንሻይን ኢንቨስትመንት ግሩፕም በገባው ውል መሠረት ደረጃውን የጠበቀ ማዕከል ገንብቷል።

ጧሪ ያጡ አረጋውያን በመጨረሻ ዕድሜያቸው የትም ወድቀው እንዳይቀሩ፤ ለምድራቸውም በረከታቸውን እንጂ እርግማናቸውን ትተው እንዳይሄዱ በሕይወት እስካሉ ድረስ እነርሱን የሚያስደስቱ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ያመላከቱት ከንቲባዋ፤ ማዕከሉን በምሳሌነት ጠቅሰዋል። ማዕከሉ ለአገልግሎት ምቹ እንዲሆንም የተለያዩ መሠረተ ልማቶች እንደተማሉለት አስረድተዋል።

አረጋውያኑ በዚህ ዕድሜያቸው በማዕከሉ ቁጭ እንዳይሉ የእደ ጥበብ፣ የግብርናና የመሳሰሉት ግብአቶችን በማሟላት ዛሬም በስራ ምሳሌ እንዲሆኑ ሁኔታዎች ተመቻችተዋል። ከዚህ በተጨማሪም ማዕከሉ የሕክምና እና የሥነ ልቦና አገልግሎት የሚሠጡ ክሊኒክ፣ መድሃኒት ቤት፣ ዘመናዊ ላውንደሪ፣ ምግብ ማብሰያና መመገቢያ እንዲሁም የመዝናኛ ስፍራዎችን ያየዘ ነው። ማዕከሉን በቋሚነት በገቢ እንዲደግፍ ከባለ ሶስት ወለል ህንፃ ኪራይ የሚገኘው ገቢ ሙሉ በሙሉ ኢጋዥ ይሆናል።

እንደ ከንቲባዋ ገለጻ፤ እንዲህ አይነቱን ሥራ ለመሥራት ልበ ቀና መሆንን ይጠይቃል። መንግሥት ብቻውን ሠርቶ የዜጎችን ጥያቄ መመለስ አይቻልም። የዜጎችን የሕይወት ጫናም ማቅለል አይቻልም። ስለዚህም የመንግስት አንዱ ሥራ እንደዚህ አይነት ሥራ ማበረታታት ነው። ባለሀብቶች ቢዝነስ ብቻ ሠርተው እንዲያተርፉ ሳይሆን ሠውን እንዲያተርፉ እና የሠውን ጫና እንዲያቀሉ ማድረግ ይገባል። ለዚህም መንግሥት ሁኔታዎችን እያመቻቸ ይገኛል።

‹‹የከተማ አስተዳደራችን የትናንት ባለውለታ የሆኑት አረጋውያንን ተገቢውን እንክብካቤ እንዲያገኙ አበክሮ እየሠራ ይገኛል። ማዕከሉ በአሁን ወቅት 80 አረጋውያንን ተቀብሎ ማስተናገድ የጀመረ ሲሆን፤ በዘላቂነትም ሌሎችን ተቀብሎ የማስተናገድ አቅም አለው።›› ያሉት ደግሞ የከተማዋ የስትራቴጂክ ፕሮግራሞች ማኔጅመንት ጽህፈት ቤት ኃላፊ ዶክተር ኢንጂነር እሸትአየሁ ክንፉ ናቸው።

በከተማ ውስጥ እንዲህ ያለውን ሥራ መሥራት እና ማቅረብ ግብ ብቻ አይደለም፤ ለታለመለት አገልግሎት እንዲውል ማድረግ ይገባል። ያንን ለማድረግም አስተዳደራዊ ጉዳይ ትኩረት ተሰጥቶት የሚሠራ እንደሆነም ከንቲባ አዳነች አቤቤ ገልፀዋል። እንዲህ ያለውን ያማረ እና ደረጃውን የጠበቀ ማዕከል በከተማዋ መገንባት በመቻሉም ለፋውንዴሽኑ ምስጋናቸውን አቅርበዋል።



አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር 30ሺ ካሬ ሜትር ላይ በ634 ሚሊየን ብር ወጪ የተገነባው ዘመናዊ የአረጋውያን ማዕከል ተመርቋል

የሰንሻይን ኢንቨስትመንት ግሩፕ ባለቤት ዶክተር ሳሙኤል ታፈሰ በበኩላቸው፤ ማዕከሉ ለአረጋውያን ምቹ በሚሆን መልኩ ተገንብቷል። ድርጅቱ እያከናወነ ካለው ኢንቨስትመንት በተጨማሪ ማህበራዊ ኃላፊነትን በሚጠይቁ ጉዳዮች ላይ ተሳትፎው ላቅ ያለ ነው። ለአብነት ያህልም በቅርቡ በአዲስ አበባ ከተማ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ነዋሪዎች በ25 ሚሊዮን ብር ወጪ የገነባውን የጋራ መኖሪያ ቤት ይጠቀሳሉ። እንዲሁም እርሳቸው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን በተማሩበት የፈለገ ዮርዳኖስ ትምህርት ቤት የዲጂታል ላይብረሪ፣ ሚኒ ሚዲያና ክሊኒክ ገንብተው ማስረከባቸውን አስታውሰዋል። ከነዚህ በተጨማሪም አነስተኛ የገቢ ምንጫ ያላቸው ልጆች፤ በተለያዩ ምክንያቶች ወላጆቻቸውን ላጡ፣ የትምህርት ዕድል ላላገኙ ታዳጊዎች እንዲሁም መማር እየፈለጉ ዕድሉን ማግኘት ላልቻሉ ዜጎች የትምህርት እድል እንዲያገኙ በበጎ አድራጎት መንፈስ በኦሮሚያ ክልል ነቀምት፣ በትግራይ ክልል አክሱም እንዲሁም በደቡብ ክልል አገና ሥራ ከጀመረ 12 ዓመታትን ማሳለፉንም ያወሳሉ። በቅርቡም በአማራ ክልል በደብረ ብርሀን ከተማ በ54 ሚሊየን ብር ወጪ አራት መቶ ተማሪዎች የሚማሩበትን ትምህርት ቤት ለምርቃት እንደሚበቃ ጠቁመዋል።

ኩባንያው ከከተማ አስተዳደሩ ጋር በመተባበር የራሱን ገቢ አመንጭቶ እስከ ሰባት መቶ ሀምሳ አረጋውያንን ማስተዳደር የሚችል፤ በሀገራችን ደረጃ የመጀመሪያ እና ሞዴል ሊባል የሚችል ዘመናዊ የአረጋውያን ማዕከል ለአገልግሎት እንዲውል የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ መድረሱንም ሥራ አስኪያጁ ይናገራሉ። አክለውም ድጋፍ ላደረጉላቸው ለወይዘሮ አዳነች አቤቤ እና ለሌሎችም ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

የከተማ አስተዳደሩ በከተማዋ ማህበራዊ ፍትህ እንዲነግስ እና ሁሉም ነዋሪዎቿ ከልማቷ ትሩፋት ተቋዳሽ እንዲሆኑ ለማስቻል ጥረት እያደረገ እንደሚገኝ ዶክተር እሸትአየሁ ገልፀዋል። እንዲህ አይነት ማዕከል በብዛት መገንባት እንደሚኖርባቸውም ያብራራሉ። ከተማችን አዲስ አበባ 5ነጥብ2 በመቶ ዕድሜያቸው ከ60 ዓመት በላይ የሆኑ አረጋውያን ይገኛሉ። ከጥቂት ዓመታት በኋላም በርካታ አረጋውያንን መንከባከብ እና መጦር እንደሚገባ አሃዞች አመላካቾች መሆናቸውን በመጠቆም፤ በከተማዋ የሚገኙ ባለሃብቶች፣ ታዋቂ ሰዎች፣ ግለሰቦች እና ድርጅቶች በእንዲህ አይነቱ ማህበራዊ ኃላፊነትን በሚጠይቅ የበጎ አድራጎት ሥራዎችን እዲቀላቀሉ ጥሪያቸውን አቅርበዋል።

# ዓለም አቀፍ

## በሕጻናት ማቆያ ክፍል በተደበቀ አደገኛ ዕጽ ምክንያት የአንድ ዓመት ልጅ ሕይወት አለፈ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አሜሪካዋ ኒው ዮርክ ግዛት በሕጻናት ማቆያ ክፍል ውስጥ ሕጻናት የሚተኙበት ምንጣፍ ስር 'ፌንታሊን' የተሰኘ አደገኛ ዕጽ በመደበቁ የአንድ ዓመት ልጅ ሕይወቱ አለፈ።

ፖሊስ ኒኮላስ ዶሚኒኪ የተባለው የአንድ ዓመት ልጅ በተኛበት የሕጻናት ማቆያ ክፍል በሽታ ብቻ የደረሰው ከመጠን በላይ ላይ የሆነ አደንዛዥ ዕጽ ምክንያት ሕይወቱ ማለፉን ቢቢሲ ከባለሙያዎች አረጋግጦ ዘግቧል።

ሕይወቱ ካለፈው ሕጻን በተጨማሪ ሌሎች በሕጻናት ማቆያው የነበሩ ሦስት ልጆች ወደ ሆስፒታል መግባታቸው ታውቋል።

ፖሊስ ዕድሜያቸው ከስምንት ወር እስከ ሁለት ዓመት የሚሆኑት ልጆች በሕጻናት ማቆያው ፌንታሊን የተባለውን እጅግ አደገኛ አደንዛዥ ዕጽ በአፍንጫቸው ስበዋል ብሎ ያምናል።



ይህን ተከትሎ ዐቃቤ ሕግ በግድያና አደንዛዥ ዕጽ ዝውውር ወንጀል ክሶች በሁለት ግለሰቦች ላይ መስርቷል።

ፖሊስ በሕጻናት ማቆያ ስፍራ ባደረገው ብርበራ ሕጻናት ከሚተኙበት ምንጣፍ ስር የተደበቀ አንድ ኪሎ ግራም የሚመዝን ፌንታሊን አግኝቷል።

የሕጻናት ማቆያ ባለቤት ዲቪኖ ኒኖና የሕንጻው አከራይ ካርሊስቶ ብራቶ የተባሉ ሁለት ግለሰቦች በቁጥጥር ስር የዋሉ ሲሆን የማንሃተን ዐቃቤ ሕግ ዳሚየን ዊሊያምስ "ተከሳሾቹ የሕጻናት ማቆያን የአደንዛዥ ዕጽ ማከማቻ በማድረጋቸው አራት ልጆችን መርዘው አንዱን ገድለዋል" ብለዋል።

የሕጻናት ማቆያ ስፍራ ሕጻናት ደህንነታቸው የሚጠበቅበት ስፍራ እንጂ ለአደንዛዥ ዕጽ የሚጋለጡበት ቦታ መሆን የለበትም ሲሉ ጨምረው ተናግረዋል።

ፖሊስ እንደሚለው ከማቆያ ቦታ የተገኘው አንድ ኪሎ ግራም ፌንታሊን 500 ሺህ ሰዎችን የመግደል አቅም አለው።

ይህ በክኒን መልክ ለሕመም ማስታገሻነት ተብሎ የሚዘጋጅ መድሃኒት 50 እጥፍ ከሄሮይን በላይ አደገኛ ሲሆን በአሜሪካ ከአደንዛዥ ዕጽ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ እየጨመረ ላለው ሞት ምክንያት ተደርጎ ይቀርባል።

እ.አ.አ. በ2010 በአሜሪካ ከመጠን በላይ የሆነ አደንዛዥ ዕጽ ወስደው ከሞቱ 40 ሺህ ሰዎች መካከል 10 በመቶ የሚሆኑት ፌንታሊን ተጠቃሚ ናቸው ተብሎ ነበር።

በ2021 ደግሞ በአደንዛዥ ዕጽ ምክንያት 100 ሺህ ሰዎች ሕይወታቸውን ያጡ ሲሆን ከእነዚህ መካከል 66 በመቶ ፌንታሊን ከመጠን በላይ የወሰዱ ናቸው።

በኒውዮርኩ የሕጻናት ማቆያ ለታዳጊው ሞትና ለሦስት ልጆች መመረዝ ክስ የቀረበባቸው ሁለቱ ግለሰቦች ጥፋተኛ ሆነው ከተገኙ ቀሪ ዘመናቸውን በእስር ሊያሳልፉ የሚችሉበት ዕድል ሰፊ መሆኑን ቢቢሲ አስታውቋል።

## በጋና ለሩሲያው ቫግነር የድጋፍ ሰልፍ አስተባብረዋል የተባሉ ክስ ተመሰረተባቸው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በጋና ለሩሲያው ቅጥረኛ ተዋጊ ቡድን ቫግነር የድጋፍ ሰልፍ አስተባብረዋል በተባሉ ግለሰቦች ላይ ክስ ተመሰረተ።

ፖሊስ ከጥቂት ሳምንታት በፊት የተዘጋጀውን የድጋፍ ሰልፍ የመሩ ናቸው ባላቸው አምስት ሰዎች ላይ ክስ መመስረቱን አረጋግጧል።

በጋና ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ በምትገኘው ታኳሪዲ ግዛት ጥቂት ሰዎች የተሳተፉበት ሰልፍ የተካሄደው የቫግነሩ መሪ የቭጌኒ ፕሪጎዢን በአውሮፕላን መከስከስ ሕይወቱ ከማለፉ 10 ቀናት ቀደም ብሎ ነበር።

በሰልፉ የተሳተፉ ሰዎች የቫግነር ቅጥረኛ ቡድንን መለያ ከነቴራ አጥልቀው እና የሩሲያ ሰንደቅ ዓላማ ሲያውለበልቡ እንደነበር የዓይን እማኞች ለቢቢሲ ተናግረዋል።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ቫግነር እንደ መካከለኛው አፍሪካ ሪፐብሊክ፣ ሊቢያና ማሊ ጨምሮ በተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት ጠንካራ ስምሪት አለው። በጋና ሰልፉን እንዳዘጋጁ የተጠረጠሩ ሰዎች በሚቀጥለው ሳምንታት ፍርድ ቤት እንደሚቀርቡ የተገለጸ ሲሆን የቀረበባቸው ክስ ይዘት በተመለከተ ግን እስካሁን የተባለ ነገር የለም።

የሩሲያው ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን ቁልፍ አጋር የነበረው ፕሪጎዢን የሚመራው የዋግነር ኩባንያ በዩክሬን ጦርነት ላይ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። ይሁንና ባለፈው ነሀሴ ወር የዋግነር ቡድን መሪ የቭጌኒ ፕሪጎዢን ተሳፍሮበት የነበረው አውሮፕላን መከስከሱ ይታወሳል።

ኢምብራየር ሌጋሲ የተሰኘው አውሮፕላን ከሞስኮ ወደ ሴንት ፒተርስበርግ ሲበር እንደነበር የሩሲያ አቪዬሽን ባለሥልጣናት አስታውቀው ነበር። አውሮፕላኑም በሰሜናዊ ሞስኮ በሚገኘው ቴቨር ክልል የመከስከስ አደጋ እንዳጋጠመውም ባለሥልጣናቱ አረጋግጠዋል።

ገር ግን ከቫግነር ጋር ግንኙነት ያለው ግሬይ ዞን የተሰኘው የቴሌግራም ገጽ ጄቱ በሩሲያ ጦር ተመትቶ መውደቁን ዘግቧል። በጋና ይህ ከመሆኑ 10 ቀናት አስድሞ ነበር ጥቂት ሰልፈኞች ድጋፍ ለማድረግ አደባባይ የወጡት።



# ስፖርት

## ‹‹ኢትዮጵያውያን ቦክስ እንችሳለን ግን ልምድ ያንሰናል››

- ቦክሰኛ ፍቅረማርያም ያደሳ

ዓለማየሁ ግዛው

በሴኔጋል ዳካር በተካሄደው የአፍሪካ ዞን የኦሊምፒክ ቦክስ ስፖርት ማጣሪያ ውድድር በ57 ኪሎ ግራም የተፋለመው ረዳት ሳጅን ፍቅረማርያም ያደሳ ሁለተኛ በመሆን የብር ሜዳለያ ማጥለቁ ይታወሳል። ውድድሩን በአስደናቂ ብቃት ያጠናቀቀው የቡጢ ተፋላሚ ይህን ውጤት ያስመዘገበው በብዙ ችግሮች ውስጥ አልፎ ነው። ያምሆኖ ፍቅረማርያም በማጣሪያው አራት ተፋላሚዎችን ያሸነፈበት መንገድ አድናቆት ያተረፈለት ሲሆን ለበርካቶችም ተነሳሽነትን የፈጠረ ነው።

ፍቅረማርያም (ጊችሮ ነብሮ) ወደ ቦክሱ ስፖርት እንዲገባ መነሻ የሆነው ተወልዶ ባደገበት አካባቢ ሀገርን መወከል የቻሉ ስመ ጥር ቦክሰኞች በመውጣታቸው ነው። ይህም ዛሬ ለደረሰበት ደረጃ ትልቅ ሚና እንዳበረከተለት ይናገራል። የአዲስ አበባ ፖሊስ ስፖርት ክለብ ቦክሰኛው በሴኔጋሉ የማጣሪያ ውድድር የገጠማቸው ተፋላሚዎች በልምድ ደረጃ ሁሉም ከኢትዮጵያውያን ቦክሰኞች የላቁ መሆናቸውን ያብራራል። ኢትዮጵያውያን ቦክሰኞች ደግሞ በሀገር ውስጥ ከሚያደርጉት ውድድር ባለፈ በዓለም አቀፍ ውድድሮች ተሳትፎ ስለሌላቸው የፕሮፌሽናል ልምድ ይጎላቸዋል ይላል ፍቅረማርያም።

ፍቅረማርያምን ጨምሮ በሴኔጋሉ ማጣሪያ የተሳተፈው የኢትዮጵያ ቦክስ ቡድን በበርካታ ችግሮች አልፎ እዚህ ደረጃ መድረሱንም የ57 ኪሎ ግራም ተፋላሚው ይጠቅሳል። እንደ ቡድን ለኦሊምፒክ ማጣሪያ የሚመጥን ዝግጅት ተደርጓል ለማለት ቢያዳግትም ተወዳዳሪዎቹ ቦክሰኞች ተስፋ ሰንቀው በስኬት ታሪካቸውን የመለወጥ ውጥን ይዘው ወደ ውድድር ይገባሉ። በዚህም አዲስ ታሪክ መጻፍ የሚችሉ ብዙዎች እንደሚኖሩ ፍቅረማርያም እምነት አለው።

ውጤት ለማስመዝገብ ቀደም ብሎ በሞሮኮና ሴኔጋል ያደረጋቸው ውድድሮች ጥሩ ልምድ እንደሆኑት ያስታወሰው የሦስት ጊዜ የኢትዮጵያ ቻምፒዮኑ ፍቅረማርያም፣ እሱ በተካፈለበት ኪሎ ግራም በቻምፒዮናው 29 ቦክሰኞች የተፋለሙ ሲሆን፤ እጅግ ጠንካራ የሆነ ፉክክር የተስተናገደበትና ወርቅ አስመዝግቦ የኦሊምፒክ ተሳታፊ ለመሆን እጅግ ፈታኝ እንደነበረ ያስታውሳል። ከተደረገው ዝግጅት በተጨማሪም በውድድሩ እጅግ ፈተኝ ሁኔታዎች መኖራቸውም ለዚህ ምክንያት እንደነበር ይናገራል።

ከጉዞ ጋር በተያያዘ የቀኑ በትክክል አለመታወቁ የቦክስ ቡድኑ ዝግጅቱ ላይ ትኩረት እንደይደረግ ተጽዕኖ ፈጥሮ ነበር። ፍቅረማርያም የነበረውን ሁኔታ ሲያስታውስም ‹‹ለነበሩት ውጣ ውረዶች ኢትዮጵያዊነቴ ጠቅሞኛል፣ ጨከን እንድልም አድርጎኛል›› ይላል። በአጠቃላይ አስቸጋሪና ፈታኝ የሚባሉ ደረጃዎችን በማለፍ የብር ሜዳሊያውን እንዳስመዘገበም ያስረዳል።

በአራቱ ዙሮች ተጋጣሚዎቹን በዝረራ፣ በነጥብና በዳኛ ውሳኔ መርታት የቻለው ፍቅረማርያም፣ የቦክስ ችሎታ ቢኖረውም በልምድ ግን ተጋጣሚዎቹ እንደሚልቁ መታዘቡንም ይናገራል። ‹‹የቦክስ ስፖርት ድብድብ አይደለም፣ ጨዋታው ማሰብን የሚጠይቅ የጭንቅላት ጨዋታ ነው›› የሚለው ፍቅረማርያም፣ ምንም እንኳን ጥሩ ውጤት ማስመዝገብ ቢችልም በተጋጣሚዎቹና በእሱ መካከል ያለው የልምድ ልዩነት እጅግ ሰፊ መሆኑን እንደተረዳ ይናገራል።



የአራቱን ዙር ውድድሮቹ በፍጹም የበላይነት በማጠናቀቅ በፍጻሜው በሶስት ዙሮች ፍልሚያ በናይጄርያዊው ቦክሰኛ ጀሸዋ አላሞ 3-2 በሆነ ጠባብ ውጤት ተሸንፎ ከኦሊምፒክ ተሳትፎ የቀረበትን ሁኔታ ሲያስታውስም ‹‹ኢትዮጵያ ለመጨረሻ ጊዜ በቦክስ ስፖርት ለኦሊምፒክ ተሳትፎ ከበቃች ረጅም ጊዜ በመቆጠሩ እንዲሁም እኔም ሀገርም ተሳትፎውን ስለምንፈልገው ትልቅ ጭንቀት ውስጥ ነበርን›› ብሏል።

እንደ ፍቅረማርያም ገለፃ፣ አፍሪካ ውስጥ ያለው የተሳትፎ እድል ማነሱ በራሱ ጉዳት አለው። በዚህም ከፍተኛ የሆነ ችሎታና ልምድ ካላቸው ስፖርተኞች ጋር ወርቅ ለማምጣት መፋለሙ አስቸጋሪ ሁኔታን ፈጥሮበታል። ተጋጣሚው ጀሸዋ በፕሮፌሽናል ደረጃ የሚጫወት ተወዳዳሪ ነው። እጅግ ጠንካራ፣ ብዙ ዙሮችን መጫወት የሚችልና ጥቂት ሽንፈቶችን ብቻ ያስተናገደም ተፎካካሪ ነው። ፍቅረማርያም ይህን ተጋጣሚ ለማሸነፍ ብዙ ሙከራዎችን በማድረግ በማድረግ ቢታገልም ተጋጣሚው ስህተት የማይሰራና ፍጹም በመሆኑ ሊሸነፍ እንደቻለ ያስረዳል።

ከውድድሩ ብዙ ልምድ በማግኘቱ ቀጣይ ለሚጠብቁት ውድድሮች ብቁ በመሆን እነሱን ማሳካት እንደሚፈልግና ጠንክሮ እንደሚሰራም ገልጿል። በመሆኑም የመጣው ውጤት የቦክስ አፍቃሪውንና ታዳጊዎችን የሚያነሳሳ በመሆኑ በውጪ ውድድሮች ልምድ ቢቀስም ኦሊምፒክን ለመሳተፍ መንገዱን እንደሚያቀለው ጠቅሷል። ብዙ ችሎታ ያለውና ብዙ የቦክስ አፍቃሪ በመኖሩ በቀጣይ ልምዶችን አዳብሮ ከዚህ በኋላ ያሉትን የኦሊምፒክ ማጣሪያዎች ማለፍ እንደሚቻልም ተናግሯል።

አሁን ያለበት ቦታ ላይ መቆም እንደማይፈልግና በኦሊምፒክ መሳተፍ ትልቅ ህልሙ እንደሆነ የሚናገረው ፍቅረማርያም፣ ለዚህም ስፖርቱ እንዲያድግ ክለቦች ቢበራከቱ፣ በባለሀብቶች ቢደግፉ እና ውድድሮች በስፋት ቢደረጉ ትልቅ ሚናን እንደሚያበረክቱ አስረድቷል። ተገቢው ሥራ የሚሠራ ከሆነ ብዙ ትላልቅ ቦክሰኞችን ማፍራት ይቻላል ብሎም ያምናል።

ፍቅረማርያም የመጀመሪያውና የልጅነት ክለቡ የኒያላ ቦክስ ክለብ ሲሆን ለቦክስ እድገቱ ትልቅ አስተዋጽኦ ሊያበረክትለት ችሏል። በኒያላ እራሱን ካጎለበተና ጥሩ እንቅስቃሴ ካደረገ በኋላ የአሁን ክለቡን አዲስ አበባ ፖሊስን ተቀላቅሏል። ክለቡ ድጋፎችን እንደሚያደርግለት አሁን ለደረሰበት ደረጃ ሚና እንዳለውም ያስረዳል። በዚህም በአህጉር አቀፍና ዓለም አቀፍ ውድድሮች እንዲሳተፍና ልምድ እንዲያካብት የክለቡ ድርሻ ትልቅ እንደሆነም ተናግሯል።